ማስታወሻ

[1] ቶማስ ጀፈርስን የአሜሪካ የመጀመሪያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፣ ሁለተኛው ምክትል ፕሬዘዳንትና ሦስተኛው ፕሬዘዳንት ነበሩ። አሜሪካውያን ከብሪታንያ አገዛዝ ነጻ መሆና ቸውን የገለጹበትንና የራሳቸውን መንግሥት የመሠረቱበትን የነጻነት ዐዋጅ (Declaration of Independence) ካረቀቁት ሰዎች መሐል ዋነኛው ናቸው። ይህ ዐዋጅ ከዓለማችን ታላላቅ ታሪካዊ ሰነዶች መሐል አንዱ ሲሆን፣ ቀጣዮቹን ሦስት መሠረታዊ ሐሳቦች አካትቷል፦

1. እግዚአብሔር ሰዎችን ሁሉ እኩል አድርጐ ፈጥሮአቸዋል። በሕይወት የመኖር፣ የነጻነትና ደስታን የመሻት መብትም ሰጥቷቸዋል።
2. የመንግሥት ዋነኛ ተግባር እነዚህን መብቶች ማስጠበቅ ነው።
3. ሆኖም መንግሥት እነዚህን መብቶች ለመግታት ከሞከረ ሕዝቦቹ ለማመፅና ሌላ አዲስ መንግሥት ለማቋቋም ነጻ ናቸው (Britannica's Concise Pictured Encyclopaedia, Volume 4 1967, p.51)።

[2] Oxford Advanced Laamer's Dictionary, Sixth Edition (Oxford, Oxford University Press, 2000).



# ስሜን ዘነጋሁት

አሉላ አባነጋ ከኢትዮጵያ ዋነኛ ጀግኖች አንዱ ናቸው። እኚህ ጀግና ከተለያዩ ጠላቶቻችን ጋር፣ በተለይም ከጣልያን ጋር ሲዋጉ ቢኖሩም፣ ድል ነስተው እንጂ ተሸንፈው አያውቁም። ስለዚህ ባሸነፉ ቁጥር በሹመት ላይ ሹመት እየተጨመረላቸው የአገር ውስጡን ማዕረግ ስለ ጨረሱት ግራ የተጋቡት ዐፄ ዮሐንስ፣ "ቱርክ-ፓሻ" እና "የራሶች ራስ" የሚሉ ሹመቶችን የሰጧቸው አስገራሚ ሰው ነበሩ።[1] ሆኖም ሞት አይቀርምና አሉላ አባነጋ ሲሞቱ፣ በፊት ያስተዳድሩት የነበረውን የአስመራ ከተማ ጣልያን ተንደርድሮ ያዘ፤ መኖሪያ ቤታቸው እንኳ አል ቀረውም - አሉላ ሞተዋላ! አሳቸው በሕይወት እያሉ ስማቸው ሲነሣ እንኳ በፍርሀት መግቢያ መውጫ ያጣ የነበረው የጣልያን ጀኔራልም ዛሬ በገዛ ቤታቸው እየኖረ ከተማዪቱን ያስተዳድር ጀመር።

ይህም አልበቃ ብሎት፣ በአሉላ ላይ ከነበረው ጥላቻ የተነሣ ውሻ ውን "አሉላ" ብሎ ሰየመ። የጣልያኑ ጀኔራል አገልጋይ የነበሩት አንድ የሐማሴን ተወላጅ ሽማግሌም የአሉላ ስም ነጋ ጠባ በዚህ ውሻ ምክንያት መለደቡ ስላንገበገባቸው፣ ውሻውን ገድለው የጀግናውን የአሉላን ስም ለማሳረፍ አሰቡ። ስለዚህ አንድ ቀን ውሻው ተኝቶ ሳለ በመጥረቢያ ብለው ገላገሉት። ጠዋት ጥልያኑ ተነሥቶ "አሉላ" እያለ ደጋግሞ ቢጣራ መልስ በማጣቱ ፍለጋ ማካሄድ ጀመረ። ያኔ ውሻው ሞቶ ስላገ ኘው "ገደልከው አይደል?" ብሎ ሽማግሌው ላይ ጮኸ (ድሮም ጥልያን መጮኽ ይወድ የለ?)። እሳቸውም፣ "ኧረ! ጌታዬ እኔ አይደለሁም! ምና ልባት ስሙ ከብዶት ሞቶ ይሆናል እንጂ" ማለታቸውን እንሰብቤያለሁ።

እስቲ አስቀድመን ስለ ስም እናውራ። ስም በማንነት ላይ ተጽ ዕኖ እንዳለው የተለያዩ የሥነ-አእምሮ ምሁራን ያስረዳሉ። ይህንን ሐሳብ መጽሐፍ ቅዱስም ያጠናክርልናል። እግዚአብሔር የሰዎችን ማንነት ሲቀ ይር ከስም ለውጥ የሚጀምረው ለዚህ ነው። አሲያማ አብራምን በአብር ሃም፣ ሦራን በሣራ፣ ያዕቆብን በእስራኤል፣ ስምዖንን በኬፋ (ጴጥሮስ) መቀየር ለምን አስፈለገ? ሳውልም ጳውሎስ ባልሆነ!

ስም ሲቀየር ማንነት (ስብዕና) የሚለወጥበት ዕድል አለ። የሥነ ልቡና ችግር የነበረበት አንድ ሰው ስሙን እንዲለውጥ ከሥነ አእምሮ ጠቢባን በተሰጠው ምክር ስሙን ሲቀይር፣ ከነበረበት ችግር ነጻ መውጣ ቱን ከአንድ የባሕር ማዶ መጽሔት ካነበብኩ በኋላ ነው ስለዚህ ጉዳይ ማሰብ የጀመርኩት። እዚሁ አጠገቤም ትምህርት አልዘልቅ እያለው የተ ቸገረ ታናሽ ወንድሜ፣ "ስሜ ተጽዕኖ አምጥቶብኛል" ብሎ በማሰቡ

የማይነገረውን ቃል” ይፋ ያደረገው ከዐሥራ አራት ዓመታት በኋላ ነው (2ቆሮ. 12÷1-5)። ሰዚያውም ግድ ሆኖበት። እኛ ግን ያየነው ነገር ሕልም ይሁን ቅዠት በቅጡ ሳናረጋግጥ፣ “ጌታ ማታ በሕልሜ የገለጠልኝን ...” በማለት እስክንናገር አያስችለንም!

ልምድ የሌለው፣ ነገሩን ብዙ ያላብላላና ከተለያየ አቅጣጫ ያላየ ሰው ሕዝብን ማስተማር የለበትም። “በሥራቸው የለመደ ልቡና ላላቸው ስፍጹማን ሰዎች” የተባለው ከዚህ የተነሣ ይመስለኛል (ዕብ. 5÷14)። ያላገባ ሰው ስለ ጋብቻ እንዳያስተምር የሚመከረው ለዚሁ ነው። ያገባስ ቢሆን በትዳር አብሮ መኖር ውስጥ ስለሚገለጡ ሁነቶች ባገባ በዓመቱ ምን ማለት ይችላል? “ትዳር የማር ስልቻ ውስጥ ገብቶ መታሰር ነው” ከሚል ስሜታዊነት የዘለለ ቁም ነገር ለመናገር የሚያበቃ ተሞክሮ ይኖረዋልን? አገልግሎት የጀመረ ሰው ገና በዓመቱ ስለ አገልግሎት ቢጠየቅስ ተገቢ ነው? በተጋቡ በመንፈቃቸው በየጋዜጣውና በየመጽሔቱ ስለ ጋብቻ እንዲያስተምሩ የሚጋበዙ ሰዎች ላይ ተቃውሞ አለኝ። “ወፌ ቆመች”ን ያላለፈ ሰው ስለ አረማመድ እንዲያስተምር “ሆይ ሆይ” ማለት የጤና ነው? “አበጃጅቶ ዳረኝ” ብለው ከሙሽርነታቸው ፎቶ ጋር በየመጽሔቱ ሽፋን ታይተው በማግስቱ ትዳራቸው እንዳይሆን ሆኖ የተፋቱ ሰዎችን እናውቃለን። ከዚያ ደግሞ ሌላዩቱን ያገቡና “እገሊት ካሳዬ ናት!” ይሉናል። አስቀድሞ ማመስገን ኋላ ለማማትም ያስቸግራል። መጽሐፍ ቅዱሳችን፣ “ባልንጀራውን በታላቅ ቃል ማለዳ የሚባርክ ሰው እንደሚራገም ያህል ነው” እንደሚል አንዘንጋ (ምሳ. 27÷14)።

የምድር ሕጐችና ሥርዐቶች ሁሉ መገኛ እግዚአብሔር እንደሆነ ታሪክ ይመሰክራል። በእርሱ ቤት ግን ሥርዐት አልበኝነት ነግሧል። “እዚህ የሥርዐት ቦታ አይደለም” የሚል ያላዋቂዎች ንግግር በመድረካችን ላይ ይደመጣል። የሚናገሩትን ካላወቁ ዝም ቢሉ እንዴት ባማረባቸው! ስለ መቅደሱና ስለ ክህነቱ ሥርዐት ያስተማራቸው የለም ማለት ነው? አፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያልና ከመናገር በፊት ቢያንስ ሁለቴ ማሰብ ይበጃል። በተለይ የሰው ስብከት እየሰሙ መዝሙራቸውን ለሚጽፉ ዘማሪዎች ስንል እንኳ ተጨማሪ ጥንቃቄ እናድርግላቸው።

“ወንድሞች ሆይ፤ ከእናንተ ብዙዎች አስተማሪዎች አይሁኑ፤ የባሰውን ፍርድ እንድንቀበል ታውቃላችሁና” (ያዕ. 3÷1)።

ማስታወሻ

[1] ከጸሐፊው ጋር በግል ካደረጉት ውይይት በፈቃድ የተካተተ።



## ሐሰተኛ የእግዚአብሔር ምስክሮች

የአሜሪካውያን የፍርድ ቤት መሐላ እጅግ ይመቸኛል። ተከሳሽ ውም ይሁን ለምስክርነት ተፈልገው ፍርድ ቤት ሲቀርቡ፣ "**I swear to tell the truth, the whole truth, nothing but the truth.**" በማለት መማል ይጠበቅባቸዋል። “እውነትንና ሙሉውን እውነት ብቻ እንጂ ከእውነት በቀር ምንም ሳልናገር እምላለሁ” ማለታቸው ነው። ለውሸት አንዳችም ክፍተት የሌለው ቃለ መሐላ ነው።

ሙሉ እውነትና ግማሽ እውነት የሚባል መኖሩን መጽሐፍ ቅዱሳችንም ይነግረናል። ለምሳሌ አብርሃም ሚስቱ ሣራን፣ “እኅቴ ናት” ማለቱ እውነት ነበር። ነገር ግን ሣራ ሚስቱም ጭምር እንጂ እኅቱ ብቻ ስላልነበረች የአብርሃም እውነት ግማሽ እውነት ነበር (ዘፍ. 20÷12)። ጌታ ኢየሱስ ግን በሚናገርበት ጊዜ ሁሉ፣ “እውነት እውነት እላችኋለሁ” በማለት ሙሉ እውነት ሲነግረን ኖሯል።

ወንጌል እውነት ነው፤ እውነት ካልሆነ ወንጀል እንጂ ወንጌል አይሆንም። ስለዚህ ሐዋርያው ጳውሎስ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ መሞቱን፣ መቀበሩንና እግዚአብሔር የሞትን ጣር አጥፍቶ ከሙታን መካከል እንዳስነሣው በደረሰበትና እግሩ በረገጠበት ስፍራ ሁሉ ይናገራል። በእርግጥ የትንሣኤው ነገር ለአንዳንዶች ማፌዣ ነበር (ሐሥ. 17÷32)። እርሱ ግን፣ “የአባቶቻችን አምላክ ኢየሱስን አስነሥቶታል” በማለት ከመናገር አልታቀበም፤ እውነት ነዋ!

ለዚህ እውነት ደግሞ ተወግሯል፤ ተርቧል፤ ተሠቃይቷል፤ ሆኖም እውነትን ከማስረዳት አልተቆጠበም። አንዳንዶች ግን፣ “ትንሣኤ ሙታን የለም” ስለሚሉ ጳውሎስ አስቀድሞ ነገሩን አሰበውና ለቆሮንቶስ ሰዎች ጻፈላቸው። “ትንሣኤ ሙታንስ ከሌለ ክርስቶስ አልተነሣማ፤ ክርስቶስም ካልተነሣ እንግዲያስ ስብከታችን ከንቱ ነው፤ እምነታችሁም ደግሞ ከንቱ ናት፤ ደግሞም ‘ክርስቶስን አስነሥቶታል’ ብለን በእግዚአብሔር ላይ ስለ መሰከርን ሐሰተኞች የእግዚአብሔር ምስክሮች ሆነን ተገኝተናል” እያለ ይዘረዝራል (1ቆሮ. 15÷12-15)።

እስተውሉ! “በእግዚአብሔር ላይ ስለ መሰከርን” ነው የሚለው። እግዚአብሔር ስላላደረገው መልካም ነገር መመስገን አይሻምና ክርስቶስ ያልተነሣ ከሆነ፣ “ከሞት አስነሣው” ብሎ በእግዚአብሔር ላይ መመስከር ሐሰተኛ የእግዚአብሔር ምስክር ያሰኛል።

በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ሌሎች ሐሰተኛ የእግዚአብሔር ምስክሮችንም እናገኛለን:: ይስሐቅ መንታ ልጆች ቢኖሩትም ከጭምቱ ከያዕቆብ ይልቅ ወንዳወንዱንና አደን የሚያዘወትረውን ዔሳውን ይወዳል፤ ልክ እንደ ሁሉም አባቶች:: ስለዚህም ከመሞቱ በፊት ሲመርቀው ፈልጎና ልጁን ጠርቶ፣ "እንደምታየው አርጅቻለሁ፤ ስለዚህ ሳልሞት እንድመርቅህ አደን አድነህ የሚጣፍጥ ምግብ አዘጋጅልኝ" አለው (ካልበሉ ምርቃት የለም እንዴ? ሴቶቹ፣ "የወንድ ልጅ ልቡ በሆዱ በኩል ቅርብ ነው" ብለው የሚያስወሩብን ለካ እውነት ነው!)::

እናትየው ርብቃ ደግሞ ቤት እየዋለ ሥር ሥሩ ለሚሄደው ወንድ ልጇ ነበር የምታደላው (የእኔን እናት ጨምሮ - የትኞቹም እናቶች ደግሞ ይኸው ናቸው):: የአባትየውን ፍላጎት የተረዳችው ርብቃ ምርቃቱን ለውድ ልጇ ለያዕቆብ ለማድረግ ፈለገች:: ስለዚህ ከልጇ ጋር በመነጋገር ከቢያው ከራሳቸው መንጋ ሁለት ጠቦቶችን አርደው ያዘጋጁትን ምግብ ያዕቆብ ወደ አባቱ ይዞ ገባ:: ይስሐቅ ፍጥነቱ አስደንግጦት፣ "ልጄ ሆይ አደኑ እንዴት እንዲህ በፍጥነት ተሳካልህ? እንዴት ቶሎ ቀናህ?" ብሎ ነበር የጠየቀው:: ያዕቆብም፣ የሚታደነውን እንስሳ "እግዚአብሔር አምላክህ ወደ እኔ ስለ አቀረበው ነው" ብሎ በሐሰት ክብሩን ለእግዚአብሔር ሰጠ (ዘፍ. 27÷20):: ያዕቆብ ሐሰተኛ የእግዚአብሔር ምስክር!

ዛሬም ይኸው ነን:: ለጥቅማችን ያሰላናት ነገር ስትኖረን፣ "እግዚአብሔር ይህን አደረገ" እያልን ሐሰተኛ የእግዚአብሔር ምስክሮች እንሆናለን:: ከእውነት ያልሆነ ምስጋና ግን በእግዚአብሔር ፊት አስጸያፊ ነው:: ምስጋናችን፣ አምልኳችንም ሆነ ስግደታችን በመንፈስ ብቻ ሳይሆን በእውነትም ሊሆን ግድ ነውና (ዮሐ. 4÷24):: ባላደረገው ነገር እግዚአብሔርን ማመስገን እግዚአብሔርን የመሳደብ (blasphemy) ያህል ነው::

አንድ ጊዜ አንድ ወንድም፣ "ጌታ የንግድ መደብር ሰጠኝ" ብሎ ትልቅ የምስጋና ፕሮግራም አዘጋጅቶ ነበር:: ብዙ ወገኖችም ተሰበሰቡና አብረውት እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ፣ ሲበሉና ሲጠጡ ዋሉ:: ሰውዬው ሱቁን በምን ዐይነት መንገድ እንዳገኘው ሲታወቅ ግን ለብዙዎች ድንጋጤ ሆነ:: በብዙ ሽፍጥና ተንኮል፣ በቅሚያ የተገኘ ንብረት ነው፤ እንባ እሰበት:: "ጌታ ሰጥቶኛል፤ ስሙ ይባረክ!" ተብሎ ግን ይመሰገናል:: እግዚአብሔር ሲታለል!?

"የትም ፍጪው፤ ምስጋናውን እምጪው" የሚል ብሂል በቅዱሱ በእግዚአብሔር ዘንድ ያለ ይመስላችኋልን? እግዚአብሔር የምስጋና ጥማት ኖሮበት፣ የቀረበለትን ምንም ዐይነት ምስጋና የሚቀበል ከሆነ፣ "አሕዛብና ሴት ስላላደረግኸኝ አመሰግንሃለሁ" በማለት በማለዳ የሚያመሰግኑ ተመጻዳቂ አይሁዳውያን ሞልተውታልና አይቸገርም::



እንደ አክአብ ናቡቴን ገድለው ዕርሻውን የወረሱ ሁሉ እግዚአብሔር "ስለ ሰጣቸው" ዕርሻ የምስጋና ፕሮግራም አዘጋጅተው እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑና ሲያስመሰግኑ ቢውሉ፣ "ገድለህ ወረስኸውን?" የሚለውን አምላካዊ ጥያቄ አይቀይሩትም (1ነገ. 20÷1-19):: መንገዳቸውን በጉቦ አሳክተው፣ "እግዚአብሔር መንገዴን አቀናልኝ" የሚሉትንም እግዚአብሔር ያውቃቸዋል::

እግዚአብሔር ዝም ቢል እኮ ሁሉን እያወቀ እንጂ ነገሩ ጠፍቶት ወይም በድርጊታችን ተስማምቶ አይደለም:: እኛ ግን አብሮን የተስማማና ነገራችንን ያጸደቀልን እየመሰለን እንሳሳታለን::

ሰዎች የተለያየ ሁኔታ ውስጥ ሲገቡና ጭንቅ ወይም ጉጉት ሲይዛቸው "ይሰማና ያድነናል" ለሚሉት አካል ስእለት ይሳላሉ:: "እንዲህ ካደረግህልኝ (ከሆነልኝ) እኔም ይህን አደርግልሃለሁ" ብለው ቃል ይገባሉ:: በተለይ የፒያሳ አካባቢ ሌቦች ለፈረሰኛው ጊዮርጊስ ነው የሚሳሉት ይባላል - ስርቆቱ እንዲሳካላቸው:: ስለዚህ ለእርሱ የተሳሉቱ ሌቦች "ሠርተው" ካገኙት ላይ ለጊዮርጊስ "ድርሻውን" ያካፍሉታል:: የሚገርመው ግን ብዙዎቻችን እግዚአብሔርን የምናየው በዚሁ መልክ መሆኑ ነው:: ሰርቀን እያካፈልነው ብንኖር ደስ ነው የሚለን:: የንስሓ ዕድል (ጊዜ) ለመስጠት ዝም ስለሚለንና ፈጥኖ ስለማይቀጣን ስለ እርሱ ያለን መረዳትና ግምት በፍጹም የተበላሸ ሆኗል:: ምንም እድርገን፣ በምንም ሁኔታ እናግኘው እርሱን ካመሰገንነውና ዐሥራታችንን ከሰጠን ዝም የምናሰኘው ይመስለናል::

እግዚአብሔርም ሆነ ምድራዊው መንግሥት በሚቃወሙት ሕገወጥ ሥራ ላይ የተሰማሩ "ክርስቲያኖች" ቁጥር ማሻቀቡ ግርታ ይፈጥራል፤ ሰዎቹ ግን የእግዚአብሔርን ይሁንታና በረከት ያገኙ ዘንድ ዐሥራት በመክፈል ገንዘባቸውን ለመቀደስ ከመሞከር ቦዝነው አያውቁም:: እርግጥ፣ የቤተ ክርስቲያን መጋቢዎችንና ሽማግሌዎችን በዚህ መንገድ ዝም ማሰኘት ተችሎ ይሆናል:: እግዚአብሔር ግን እንዲህ ይላል፤ "ሌባውን ባየህ ጊዜ ከእርሱ ጋር ተሮጥ ነበር፤ ዕድል ፈንታህንም ከአመንዝሮች ጋር አደረግህ ... ይህን አድርገህ ዝም አልሁህ፤ እኔ እንደ አንተ እሆን ዘንድ ጠረጠርህ" (መዝ. 50÷18-21)::

እግዚአብሔር ዝም ሲለን ደግሞ እርሱ ራሱ የእኛ ቢጤ ይመስለን ጀምሮአል፤ እውነቱ ግን ከዚህ የተለየ ነው:: መጽሐፍ ቅዱሳችን፣ "አቤቱ መንገድህ በመቅደስ ውስጥ ነው" ይላልና (መዝ. 77÷13) እግዚአብሔር ያሰበት ነገር ውጤቱ (ግቡ) ቅዱስ የሆነውን ያህል መንገዱም ቅዱስ ነው ማለት ነው:: ቅዱስ ባልሆነና በረከሰ መንገድ የተገኘን ነገር፣ "እግዚአብሔር አደረገልኝ" ማለት አይቻልም:: ፈረንጆቹ፣ "The end justifies the means." ይላሉ፤ "ዋናው ውጤቱ ነው" እንደ ማለት ነው:: የእግዚአብሔርን ነገር በተመለከተ ግን ትክክለኛው አባባል፣ "The

በአንድ ኮንፈረንስ ላይ ጥቂት ሰዎች ጌታን ለመከተል ሲወስኑ፣ “ከተማዋ ሙሉ በሙሉ ለጌታ እጅ ስጠች (ተማረከች)” ብለው ያት ማሉ:: "Time" እና "Newsweek" በመሳሰሉ የፈረንጅ መጽሔቶች ላይ የወጡ የመካከለኛውና የሩቅ ምሥራቅ ሰዎችን ምስል በመጠቀም፣ ክክር ስቶስ ተቃዋሚነት ወደ ክርስቶስ ተከታይነት እንደ ተለወጡ አድርጐ ድርሰት የሚያወጣ መጽሔትም ዐውቃለሁ:: አዘጋጁ ብዙ ተቃውሞ ቢቀርብባቸውም፣ “ካፈርኩ አይመልሰኝ” ያሉ ይመስል፣ የንግድ ዘይቤያ ቸውን ማስተካከል አልፈለጉም:: እዚህ ላይ የሚሰደበው የአምላካችን ስም በመሆኑ ሁላችንም ኀላፊነት አለብን:: አንባቢዎችም ቢሆኑ፣ “አትን ኩብን” በማለት በጭፍን ተፎዞነት ከሚሰለፉ፣ ግለሰቡን ከዚህ ስህተት ለማውጣት እጃቸውን ቢዘረጉ ለእግዚአብሔር መቅናታቸውን በተግባር ባረጋገጡ ነበር:: ስለዚህ፣ “ከጨለማ ሥራ ጋር አትተባበሩ፤ ይልቁን ግለጡት እንጂ” የሚለውን ቃል እንዲያነቡት በትሕትና እመክራለሁ (ኤፌ. 5÷11)::

“ሰዎች እነዚህን ምስክርነቶች አንብበው ወደ ጌታ እየመጡ በመ ሆኑ፣ ውሸትስ ቢሆን ምን ክፋት አለው?” የሚል ጥያቄም ተነሥቶ ነበር:: ሰዎች በእውነት ቃል ተወልደው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ይጨመሩ ዘንድ የውሸት ምስክርነት መጠቀም የሚያሥቅ (ridiculous) ብቻ ላይሆን የሚያሳፍርም ነው:: ገጣሚና ጸሓፌ ተውኔት ጌትነት እን የው “የማይቻል አንድ ነገር” በሚል ርእስ ያቀረበው ምርጥ ግጥም ይህ ንን በደንብ የሚገልጸው ይመስለኛል::

“እውነት ቤት ስትሠራ
ውሸት ላግዝ ካለች
ጭቃ ካራገጠች
ምስማር ካቀበለች
ቤቱም አልተሠራ
እውነትም አልኖረች::” [1]

ውጤቱ የተቀደሰ እንዲሆን መንገዱም የተቀደሰ ሲሆን ያስፈል ጋል:: ማስታረቅ በጐ ክርስቲያናዊ ተግባር ነው - ዋሽቶ ማስታረቅን ግን እኔ የማነብበው መጽሐፍ ቅዱስ አይደግፈውም:: ማስታረቅ መልካም ቢሆንም ውሸት ግን የረከሰ ነው::

እንግሊዞች ሮቢን ሁድ ስለሚባል አስገራሚ ወንበዴ አፈ ታሪክ አላቸው:: ሽፍታው ሮቢን ሁድ ባለጠጋዎችን ይዘርፍና የዘረፈውን ለድኾች ያከፋፍል ነበር:: ልክ እንደ እርሱ፣ እየዘረፉ ለእግዚአብሔርና ለተቸገሩ ሰዎች ለመስጠት የሚዳክሩ መንፈሳዊ “ሮቢን ሁዶች” አጋጥ መውኝ ያውቃሉ:: ድኻን መርዳት የተቀደሰ ተግባር ቢሆንም ዝርፊያ ግን ኀጢአት ነው፤ የተቀደሰውን ከረከሰው ጋር አዛምዶ “ቅዱስ ኀጢ አት” ማበጀት ደግሞ አይቻልም::



እውነት ካልሆነ ወንጌል ሊሆን አይችልምና:: የሐሰት አባት ደግሞ ዲያ ብሎስ እንደሆነ ጌታ ኢየሱስ ነግሮናል (ዮሐ. 8÷44)::

“ጥቂቶችን ሁልጊዜ ማታለል ይቻል ይሆናል:: ሁሉንም ሰው ለጥቂት ጊዜ ማታለልም ይቻላል:: ሁሉንም ሰው ሁልጊዜ ማታለል ግን በፍጹም አይቻልም::” (አብርሃም ሊንከን)

ማስታወሻ

[1] ጌትነት እንየው፤ *ዕውቀትን ፍለጋ* (አዲስ አበባ፤ 1994) ገጽ 26::

# “እግዚአብሔር ምን ነካው?”

ወቅቱ አዲስ ዓመት ሲሆን፣ ቦታውም ትምህርት ቤት አካባቢ ነው:: ተማሪዎች ለዓመቱ የተመደበልንን ትምህርት ለመጀመር ቀዳሚውን ምዝገባ አካሂደን ገና መጨረሳችን ነው:: ያው እንደተለመደው ሁለቱን የክረምት ወራት ሳንገናኝ በመክረማችን ናፍቆታችንን ለመወጣት አንዱ ጥግ ተሰባስበን እንጨዋወታለን:: ብዙ ብዙ ጉዳዮችን ስናነሣና ስንጥል ቆይተን፣ ሳናስበው ጨዋታው የአዲስ ዓመት ዕቅዶቻችንን ወደ መወያየት አዘነበለ:: እያንዳንዱ የየራሱን ተናገረ፤ የሁሉም የተለያየ ነው፤ ለማግባት ያቀዱ ግን በርክት አሉብኝ:: “እግዚአብሔርን ለማሣቅ ትፈልጋለህ? እንግዲያውስ የወደፊት ዕቅድህን ንገረው” የሚለው የአሜሪካዊው የኮሜዲ ፊልም ተዋናይና ዳይሬክተር የዉዲ አለን ንግግር ትውስ አለኝና መገረም ጀመርኩኝ::

ገና አግራሞቱን ሳልጨርስ አንዷ ድንገት ወደ እኔ ዞራ፣ “የአንተስ ዕቅድ?” ብላ አፋጠጠችኝ:: “የእኔ ዕቅድ” አልኩና ጀመርኩ፣ እንዴት እንደምገልጽላቸው እያሰብኩ:: የጠየቀችኝ እርሷ ብትሆንም ሁሉም የእኔን ምላሽ እየጠበቁ መሆኑ ገብቶኛል:: “የእኔ ዕቅድ፣ ... በቃ መኖር ነው” በማለት ተናገርኩ:: ሁሉም የሆነ ነገር ገባቸው - ግራ ገባቸው:: “ምን?” አለች ጠያቂዬ፤ ብትሰማኝም ማረጋገጥ የፈለገች ይመስለኛል:: “መኖር!” አልኩ ፍርጥም ብዬ:: ያኔ እርግጠኛ ስለሆነች ምላሽ ለመስጠት አልተቸገረችም:: “ወደህ ነው? የግድህን ትኖራታለህ!” ነበር መልሷ:: ጨዋታውን ጨርሰን ከተለያየንም በኋላ ድምጿ ከጆሮዬ አልጠፋም:: “ወደህ ነው? የግድህን ትኖራታለህ!” ይለኝ ነበር ደጋግሞ::

ግን የግዳችንን ነው እንዴ የምንኖረው? ቆይ የአንድ ሌላ ጓደኛዬ አባባል ትዝ አለኝ:: “ኡፍ አሁንስ መኖር ደከመኝ፤ ለአንድ ሁለት ወር ሞቶ መመለስ ቢቻል ምናለበት?!” ይለኛል ብዙ ጊዜ:: ያኔ ሕይወት እንደ ታከተው ይገባኛል:: በእርግጥ ሁለት ወር የምትለዋ የጊዜ ገደብ እንደየሁኔታው ከፍ ዝቅ ትላለች:: በጣም ሲከፋው፣ “ለአንድ ለስድስት ወር ብቻ መሞት ቢቻል!” ይላል:: አምብዛም ካልከፋው ደግሞ፣ “ለአንድ ለዐሥራ አምስት ቀን!” ይሆናል ምኞቱ:: መሞትን ቢመኝም መመለስ መኖሩን አረጋግጦ ነው - ሕይወት አይደል?

ስመሆኑ ሕይወትን እንዲህ ግራ አጋቢና እንደ ነብር ገላ ዝንጉርጉር ያደረጋት ምን ይሆን? ለዚህ ብዙ ሰበቦችን መጥቀስ ይቻላል:: ሰዎች ያሰቡት አልሳካ ሲላቸው፣ የጠበቁት ሳይሆን ቀርቶ ያልጠበቁት



ሲከሰት፣ ጥረው ግረው ክልፋታቸው ውጤት ሲታጣ ሕይወት ግራ አጋቢ ትሆንባቸዋለች፤ መኖርም ይደክማቸዋል:: በጌታ ያላረፉትስ የሕይወት ካርታ ሲጠፋባቸው፣ ከእነርሱ ይልቅ ስለ እነርሱ ወደሚያውቅላቸው ጌታ መጥተው ክጥላው በታች እንዲጠለሉ ይመክራሉ:: ግና ሕይወት እየመረረችው ያለው ክርስቲያኑ ከሆነስ ምን ሲባል ነው? ብዙውን ጊዜ የሚገርመኝ ነገር አለ፤ ክርስቲያኖች የሆነ ነገር አልሆን ባላቸውና በተበላሸባቸው ጊዜ ከእግዚአብሔር ራስ አለመውረዳቸው! “ታዲያ ምኑ ነው ያስገረመህ!” አትሉም? ሰዎቹ ትክክል መሆናቸው ነዋ!

እኛ ለራሳችን መኖር ሲያቅተን፣ “አንተው ኑርልን፤ የሕይወታችንን መሪ አንተው ያዝና ወደ ወደድከው ምራን” ብለን እጃችንንና ልባችንን ስለ ሰጠነው፣ ነገሮች ትርምስምስ ሲሉብን ወደ እርሱ ብንመለከት አልተሳሳትንም::

የሁላችንም ጥያቄዎች ለየቅል ቢሆኑም፣ መንስኤው ተወራራሽ ሆኖ የሚገኝባቸው አጋጣሚዎች ጥቂት አይደሉም:: ይህንን ስል፣ የሕይወትን ግራ ገብነት ምስጢር በአንድ ለመፈረጅ መቻል ይቅርና ማሰብ እንኳ አዳጋች እንደሆነ ስቼው አይደለም፤ ከችግሩ ክምር መሐል አንዱን ምክንያት (ምናልባትም አንኳሩን) መዝዘን እንድናይ ፈልጌ እንጂ::

አንዳንድ ሰው ለራሱ አልሆን ስላለው ብቻ ሳይሆን አጠገቡ ያሉ ወይም በርቀት የሚያውቃቸው ኀጢአተኞች ሲሳካላቸው ሲያይ፣ በእግዚአብሔር ርትዓዊነት (ጻድቅነት) ላይ ያለው ልበ ሙሉነት ጥያቄ ውስጥ ይገባና ሕይወትን መጥላት ይጀምራል፤ የሕይወት መልክ በእግዚአብሔር መልክ ይወሰናልና! ስለዚህ እግዚአብሔር እንደ ተሳሳተ ወይም የሚሠራው ልክ እንዳልሆነ ማሰብ ይጀምራል:: “እንዴ፣ እግዚአብሔር ምን ነካው?” ያለኝን ቀን ወንድም መቼም የምረሳው አይመስለኝም:: እናም ከዚህች እንደ ጥላ ከምታልፍ እንፋሎት ዘመናቸው ያገኙትን የሕይወት ልምድ ተደግፈው በዘመናት ለሸመገለው እግዚአብሔር ምክር ለመስጠት ይቃጣቸዋል::

በዚህ ጊዜ ነው እግዚአብሔርን ስለ አሠራሩ ዳኛ ፊት ቢያቆሙት እንደሚረቱት፣ ይህም ባይሆን እንኳ ሲሞግቱት እንደሚችሉ ሰዎች አስረግጠው ማሰብ የሚጀምሩት:: ግን የት ያግኙት? መኖሪያው ሰማይ! ኢዮብ ትዝ ይላችኋል? “እርሱን (እግዚአብሔርን) ወዴት እንዳገኘው ምነው ባወቅሁ! ወደ ተቀመጠበትስ ስፍራ ምነው በደረስሁ! በፊቱ ሙግቴን አዘጋጅ ነበር፤ አፌንም በማስረጃ እሞላው ነበር” የሚል ነበር የኢዮብ ምኞት (23÷2-5):: ለነገሩ እግዚአብሔር ተወራርዶበት፣ እንዲያ የከፋ ሁኔታ ውስጥ የገባ ሰው ይህን ቢናገር፣ “እንዴት እንዲህ ደፍረህ ትናገራለህ!” ብላችሁ ትቆጡት ይሆን?

ከላይ እንደ ቀላል የጠቀስነው የኀጢአተኛ መለምለምና የጻድቁ የጠወለገ መምሰል የእኛ ብቻ ሰሞነኛ ጥያቄ አይደለም፤ ብዙ ትልልቅ

የእግዚአብሔር ሰዎችም ግራ በመጋባት የሰነዘሩት ዘመን ዘለቅ ተደጋ
ጋሚ ጥያቄ እንጂ:: "ጻድቅና ፍጹም ሰው መሳለቂያ ሆኖአል:: ... የቀማ
ኞች ድንኳን በደኅንነት ይኖራል፤ እግዚአብሔርንም የሚያስቆጡ ተዘል
ለው (ያለ ስጋት) ተቀምጠዋል፤ እግዚአብሔር ሁሉን በእጃቸው አምጥቶ
ላቸዋል" (ኢዮብ 12÷4-6):: ኢዮብ በዚህ ብቻ አላበቃም፤ የምዕራፍ
21÷7-15 ሐሳብም ተመሳሳይ ነው:: በተለይም፣ "... የእግዚአብሔርም
በትር የለባቸውም" የሚለው ቁጥር 9 ላይ ያለው ቃል ያስቀናል:: መዝ
ሙረኛውም፣ "እነሆ እነዚህ ኀጢአተኞች ይደሰታሉ፤ ሁልጊዜም ባለጠግ
ነታቸውን ያበዛሉ::" አለና የራሱ በቅድስናና በጽድቅ መኖር ብድራቱ
አልታይ ሲለው ቀጠል በማድረግ፣ "በውኑ ልቤን በከንቱ አጸደቅሁ፤
እጆቼንም በንጽሕና በከንቱ አጠብሁ" ለማለት ቃጥቶታል (መዝ.
73÷12-13):: ኤርምያስስ ቢሆን፣ "የኀጢአተኞች መንገድ ስለ ምን ይቃ
ናል? በደልንስ ለሚያደርጉ ሁሉ ስለ ምን ደኅንነት ይሆናል? ተክለሃቸ
ዋል፤ ሥር ሰድደዋል፤ አድገዋል፤ አፍርተውማል" (ኤር. 12÷1-2)
እያለ ይሞግት የለም እንዴ? ታዲያ ሰዎች ዛሬም ይህን ቢጠይቁ ምን
ያስገርማል?

ሰዎች የእግዚአብሔር አሠራር ኀጢአተኛን የሚሸልም ሲሆንባ
ቸው እንዲህ ዐይነቱ ጥያቄ ቢፈጠርባቸው አያስደንግጥም:: ከዚህም የተ
ነሣ "ጽድቅ ምን ይሠራልኛል?" ለማለት የደፈሩና የእግዚአብሔር አሠ
ራር አልጥም ያላቸው ጥቂቶች አለመሆናቸውን ለመረዳት አካባቢያችሁን
በውል ማጤን በቂ ይመስለኛል:: ይህ እኮ ቀላል ጉዳይ አይደለም፤
ሰዎች ደፍረው በእግዚአብሔር ላይ እንዲናገሩ ከሚገፋፏቸው ነገሮች
ዋነኛው ነው:: አንዱ በዚሁ የእግዚአብሔር አሠራር ግራ ተጋብቶ፣
"እግዚአብሔር አረጀ ወይ?" ሲለኝ ድፍረቱ አላስደነገጠኝም፤ አለመደን
ገጤ አስደነገጠኝ እንጂ!

አንዴ እንዲህ ዐይነቱ ምርምር ውስጥ ከገባችሁ ደግሞ ያስፈ
ራል:: ይህ ውጥረት በራሱ ያነሰ ይመስል ከምድር ይውጡ ከሰማይ የማ
ይታወቁ ወፈ-ሰማይ ጥያቄዎች በእናት በእናት እየተረባረቡ ነፍሳችሁን
ያስጨንቁታል:: አንዳንድ ይህንኑ ጥያቄያችሁን የሚያጉሰብቱ ክስተቶ
ችም ሊያጋጥሟችሁ ይችላሉ:: ሼክስፒር፣ "ሐዘን ብቻውን አይመጣም፤
ሰራዊቱን ሁሉ ይዞ እንጂ" (When sorrows come, they come not
single spiee, But in battalions!)[1] ያለው ለዚህም ይሠራ ይሆን?

ብቻ ሙሉውን ቀን በጥያቄ ተወጥራችሁ ቁና ቁና ስትተነፍሱ
ትውላላችሁ:: ሰው ይሥቃል፣ ይጫወታል፤ እናንተ ጥያቄያችሁን ታመ
ነዥጋላችሁ:: ምናልባት አንዳንዴ የእግዚአብሔርን መልካምነትና ፍቅር
ማየት እንኳ ሊያቅታችሁ ይችል ይሆናል:: ታዲያ በዚህ ጊዜ ዕራቁታች
ሁን አውላላ ሜዳ ላይ እንደ ቆማችሁ ዐይነት ስሜት ይፈጠርባችኋል::
ከዚያ በቃ ውስጣዊ ዕረፍትና ሰላም ስለሚጠፋ እንደ ወተት ሲናጡ



መክረም ነው:: የሚያስደስታችሁም ነገር ስስምታጡ ያነጫንጫችኋል::
አሁን የምትኖሩት ሕይወትም ከዚህ በፊት የኖራችሁት አሮጌ ሕይወት
ይሆንባችኋል:: ጠዋት ምጥ፣ ማታ ምጥ! የየቀኑ ለውጥ አልባ ድግግ
ሞሽ ኑሮ ትክት ይላችሁና እንደዚያ ወዳጄ፣ "መኖር ደከመኝ፤ ምናለ
የሆነ ጊዜ ተሙቶ መመለስ ቢቻል!" ለማለት ይዳዳችኋል:: መመለስ
የምትለዋን ቃል ግን አትረሷትም!

ሕይወት እንዲህ ጣዕም አልባና እንቶቅልሽ ስትሆን፣ ምናልባት
ከዛሬ ነገ ሁኔታዎች ተቀይረው እመለከት ይሆን? ብላችሁ ብትጠብ
ቁም፣ በምትጠብቁት ፍጥነት አንዳች ፋይዳ ያለው ነገር ዐይናችሁ አላይ
ይላል:: ስለዚህ አዲሰ ቀን ወገግ ባለ ቁጥር ውስጣችሁ (ሆዳችሁ አባል
ኩም) "እረ የአዲስ ነገር ያለህ?" እያሰ ይጮኻል::

መልሱ ደግሞ አንድ ነው - እግዚአብሔር! "በዙፋኑም የተቀመ
ጠው 'እነሆ ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ' አለ:: ለእኔም 'እነዚህ ቃሎች የታ
መኑና እውነተኞች ናቸውና ጻፍ' አለኝ" (ራእይ 21÷5)::

ነገር ከማበዛ እግዚአብሔር እንዲህ የሚያደርግበትን ምክንያት
ለማየት እንሞክር:: መቼም የዚህን ከባድ ጥያቄ አጠቃላይ ምላሽ ለመስ
ጠት ባልደፍርም፣ በራሴ አተያይ ሦስት ምክንያቶችን ለማቅረብ እሞክራ
ለሁ::

አንደኛው የእግዚአብሔርን ባለሥልጣንነት ያሳያል:: እግዚአብ
ሔር ልካችሁን እንድታውቁ ሁሌም ይፈልጋል:: ራሱ እግዚአብሔር
የፈጠረውን ዓለም ራሱ በወደደው መንገድ ነው ማስተዳደር ያለበት::
በእርሱ አገዛዝ ላይ ተቃውሞ ለማንሣት እናንተ ማን ናችሁ? እግዚአብ
ሔር ይህ በደንብ እንዲገባችሁ ይፈልጋል:: በምንም መንገድ ፈቃዱ ይፈ
ጸማል፤ ሐሳቡ ይጸናል:: በመነጫነጭ፣ በማባበል፣ በመለማመጥና አን
ጀት በመብላት (በማስተዛዘን) የሚሆን አንዳች ነገር የለም:: "እርሱ ግን
ብቻውን ነው፤ እርሱንስ የሚመስለው ማን ነው? ነፍሱም የወደደችውን
ያደርጋል:: በእኔ ላይ የተወሰነውን ይፈጽማል፤ እንደዚህም ያለ ብዙ
ነገር በእርሱ ዘንድ አለ" (ኢዮብ 23÷13-14):: ኢዮብን የጠቀስኩት ያለ
ምክንያት አይደለም:: የእኛኑ ዐይነት ጥያቄ በማንሣቱ ከጉናችን አስልፈ
ነው ስለነበር የእርሱ ንግግር ይበልጥ ይገባናል ብዬ ነው:: ከእርሱ በፊት
እምላክ ስለሌለ ማንም እግዚአብሔርን፣ "ለምን እንዲህ ታደርጋለህ?"
ሊለው አይችልም:: ይህም ቢባል ግን እግዚአብሔር በምንም መልኩ
አምባገነን ገዢ አይደለም:: ከእኛ የበለጠ ማወቅ ብቻ ሳይሆን፣ ስለሚያ
ውቅልንም በፍቅር ነው የሚገዛን:: ደግሞ እርሱ እግዚአብሔር ነውና
ደስ ያለኘውን ያደርጋል፤ በሰማይና በምድር መካከል ያሰበውን ይፈጽ
ማል:: በቃ!

ሁለተኛው ደግሞ የእግዚአብሔርን ዐዋቂነት ያመለክታል::
እርሱ በመጀመሪያ መጨረሻውን ያውቃል (ኢሳ. 46÷10):: ስለዚህ እና

ንተ ራሳችሁን ከሌላው ጋር እያወዳደራችሁ፣ "እንዴት እንዲህ ሆነላቸው?" ብላችሁ በኀጢአተኞች መስምስም እየተብስከሰካችሁ ዐይናችሁ ቢቀላም፣ መሰስ ስትሉ በበታቸው የሉም፤ መታስቢያቸውም ጠፍቷልና ብትፈልጉም አታገኙአቸው:: መዝሙረኛው ቀደም ብሰን ካየነው ተመሳሳይ ጥያቄው ቀጠል አድርጐ፣ "... በድጥ ስፍራ አስቀመጥኻቸው፤ ወደ ጥፋትም ጣልኻቸው:: እንዴት ስጥፋት ሆኑ! በድንገት አሰቁ ስሰ ኀጢአታቸውም ጠፉ..." ያስው ስዚህ ነው (መዝ. 73÷15-20)::

እርስ ደግሞ ሁሌም ትክክል ነው:: ስምሳሌ በኢዮብ ጉዳይ ላይ ኢዮብ በአንድ ወገን፣ የኢዮብ ወዳጆች ደግሞ በሌላ ወገን ሆነው ሲፋስጡ እንደ ቆዩ ብዙዎቻችሁ ታውቃላችሁ ብዬ አስባለሁ:: ያኔ ከእግዚአብሔር ይልቅ ራሱን ጻድቅ አድርጐ የነበረው ኢዮብ (32÷2)፣ ኋላ ላይ መሳሳቱ ግልጽ ሆነ:: ስዚህም የኋላ ጸጸቱ በቂ ምስክር ነው (42÷5-6):: "እግዚአብሔር ተሳስቷል!" ይል የነበረው ኢዮብ ስህተቱን ተረድቶ ከተጸጸተ፣ "እግዚአብሔር ልክ ነው!" ባዮቹ የኢዮብ ወዳጆች ልክ ናቸው ማስት ነው - በእኛ መረዳት:: ሆኖም እነርሱም ተሳስተዋል ተባለ:: "እግዚአብሔርም፣ ቴማናዊውን ኤልፋዝን 'እንደ ባሪያዬ እንደ ኢዮብ ቅንን ነገር ስለ እኔ አልተናገራችሁምና ቁጣዬ ... ነድዶአል:: ... ባሪያዬም ኢዮብ ስለ እናንተ ይጸልያል፤ እኔም እንደ ስንፍናችሁ እንዳላደርግባችሁ ፊቱን እቀበላለሁ' ..." (42÷7-8):: ታዲያ ሁሉም ወገን ከተሳሳተ ትክክሉ ማነው? እግዚአብሔር ብቻ ነዋ!

እግዚአብሔር ብቻ ሁሌም ትክክል ነው:: "እንዴት ይህ ሆነብኝ?" በማለት ስታፈጥጡ እርሱ ወይ ከሚመጣው አደጋ ሲታደጋችሁ፣ ካልሆነም የምትፈልጉትን ነገር እጃችሁን መትቶ ያስጣላችሁ ሲጠቅማችሁ - ለእናንተው አስቦ ነው፤ ስራሱም ደግሞ አስቦ ነው - እንዳትጠፉበት (ዕድል ፈንታው እናንተ ናችሁ!):: እኔም አንዴ በሆነብኝ ነገር የእግዚአብሔር አሠራር ግራ ገብቶኝ ስነጫነጭ ቆየሁ (ተነጫንጬ ምንም እንደማላመጣ ግን ጠንቅቄ ዐውቃለሁ):: ብወራጭ ብፈራገጥ ወይ እቴ! እርሱ ፍንክች ሊል ነው? እንዲህ እንዲህ ስንሆን ጥቂት ጊዜ ዐለፈና ነገሮች ትክክለኛ ቀስማቸውን መያዝ ሲጀምሩ ሁሉ ነገር ፍንትው ብሎ ታየ:: ለስማችን እንኳ የሚጠነቀቅ አምላክ ነው ያለን:: ለካ አልገባኝም እንጂ እየታደገኝ ነበር:: ይህንን ላይ በጥበቡ እየተደነቅሁ፣ ጥበብ በማጣቱ ተጸጸትኩ:: አቤት ከኩርፊያ በኋላ ያለ ፍቅር! (ይህንን አፍቃሪዎች ብቻ ነው የሚያውቁት::)

ሦስተኛው ምክንያቱ ደግሞ ዐይናችንን ከአይረቤው ምድራዊ ነገር ላይ እንድንነቅልና አሻግረን እንድናይ ስለሚሻ ነው:: ለዘላለሙ ክብር የተጠራን ቅዱሳን፣ "ኀጢአተኛው ስመሰመ፤ እገሌ ከስመነ" በማሰት ስምድራዊው ስኬት ስንዳክር ዘመናችን መባከኑን ጌታ አይወደውም:: በሚቀጥለው ዓለምና ዘመን ብቻ ሳይሆን፣ በምድርም ላይ ፍሬ



እንድናፈራ ይፈልጋል:: ስለዚህ ቅርንጫፉን ያጠራዋል:: ከዚህም አልፎ ተስፋችን የከበረና ሞትን የሚያሻግር፣ ከሞት በኋላ ፀሐይ የሚያወጣ ነው! የትኛውም ስኬት ከመቃብር ጉድጓድ አያልፍም:: ዝና፣ ገንዘብ፣ ሥልጣን ... ሞትን አያሸንፉም:: ስለዚህ በላይ ያለውን እሹ:: የፈለገ ዕቅድ ቢኖረን እና ዕቅዳችን ቢሳካልን፣ ለስንት ዓመት የሚዘልቅ ክብር ይሆን? ሃያ፣ ሠላሳ ወይስ አርባ? እግዚአብሔር ግን የዘላለም ክብር ነው ያዘጋጀልን!

አብርሃም ዕድሜ ዘመኑን በድንኳን የፈጀው ቤት የመሥራት ጥበቡ ሳይገባው ቀርቶ አይደለም:: እንኳን እርሱ፣ ተከትሎት የወጣው ሎጥም ቤት ነበረው (ዘፍ. 19):: አብርሃም ግን "ሎጥ ስመሰመ፤ እኔ ጠወለግሁ" አላለም:: "መሠረት ያላትን እግዚአብሔር የሠራትንና የፈጠራትን ከተማ ይጠብቅ ነበረና" (ዕብ. 11÷9-10):: ይህ እውነታ ወደ መንፈሳችሁ ይዝለቅ:: ሐዋርያው ጳውሎስም የሚለን እሰው፤ "በዚች ሕይወት ብቻ ክርስቶስን ተስፋ ያደረግን ከሆነ ከሰው ሁሉ ይልቅ ምስኪኖች ነን" (1ቆሮ. 15÷19):: ይህ እንዲገባን እግዚአብሔር የያዝነውን ያስጥለን ይሆናል - ተስፋችን በዚህ ምድር ስላልሆነ:: ኀጢአተኞች ደግሞ ለጊዜው ይባረኩ ይሆናል - ተስፋቸው በዚህ ምድር ብቻ ስለሆነ:: ቆይ ቆይ፤ እኛ ምስኪኖች ነን እንዴ? ስለ እናንተ ራሳችሁ ታውቃላችሁ፤ እኔ ግን ምስኪን አይደለሁም! ምክንያቱም ሁልጊዜ ከፊቴ ዘላለማዊ ተስፋ ፍንትው ብሎ ይታየኛልና!

<u>ማስታወሻ</u>

1. *The Complete Works of William Shakespeare (London. Spring Books, 1970) p.971.*

## “አቤቱ አታለልከኝ፤ እኔም ተታለልሁ”

በአንድ ወቅት የሰማሁትን ታሪክ ልንገራችሁ፤ አንድ ወንድም
ስለ አንድ አገልጋይ ራእይ አይቷል። አገልጋዩ ከአንዲት ቤተ ክርስቲያን
ጋር በገመድ መቆራኘቱን ነበር ያየው። ልክ ይህንን እንዳየ መልእክቱን
በራሱ መረዳት ይተረጉምና ለባለመልእክቱ ያስተላልፋል፤ ለአገልግሎት
እንዳይዘረጋ ሩጫውን በሚገድብ መልክ መታሰሩን አጠንክሮ ያስገነዝበ
ዋል። “በል እንግዲህ ተቃውመህ የታሰርክበትን በጥሰህ ሂድ” ብሎ
ይመክረዋል፤ ይጸልይለታልም። ኋላ ላይ መልእክት ተናጋሪው ወደ ቤቱ
ሲሄድ ግን ጌታ ስለተናገረው ትርጉሙ ሲገባው ይደነግጣል። ለካ ጌታ
ራእዩን አሳየው እንጂ ትርጉሙ ሌላ ነው። ጌታ ለማለት የፈለገው ይህ
ንን አገልጋይ ከዚያች ቤተ ክርስቲያን ጋር በአገልግሎት ማቆራኘቱን፣
የአገልግሎት ስፍራው እዚያው ቦታ መሆኑን ሲያስምርበት ፈልጐ ነው።
እግዚአብሔር የተናገረውና ሰዎቹ የተረዱት የተለያየ መሆኑ ምንኛ
ያሳዝናል!

ለመናገር ያሰብኩት ስለ አገልጋዮች ስህተት አይደለም፤ ጉዳዩ
ሌላ ነው። ዛሬ ዛሬ ብዙ ወገኖች በከፍተኛ ግራ መጋባትና ሐዘን ተው
ጠው አያለሁ። እግዚአብሔርን ያኮረፉማ በየቀኑ ነው የሚያጋጥሙኝ።
ለነገሩ ልጅ አባቱን የማኩረፍ መብት እንዳለው ማን ይክዳል? አባትም
እንደየሁኔታው ያባብላል፤ ይገሥጻል፤ ይቆጣልም። በእርግጥም ክርስቲ
ያን ከሐዘኑም ሆነ ከደስታው፣ ከጉስቁልናውም ሆነ ከበረከቱ፣ ከውድቀ
ቱም ሆነ ከስኬቱ ጋር የሚያያዝ የልብ ሐሳቡን ከእግዚአብሔር ጋር ማገ
ናኘቱ ግድ ይመስለኛል። የእኛ ጉዳይ፣ የእኛ ዕጣ በአብዛኛው ከእርሱ
ጋር የተሳሰረ ነውና!

እነዚህ ከላይ ያነሣኋቸው በርካታ ክርስቲያኖች ዋነኛ ሐዘናቸው
የእግዚአብሔር ተስፋ መዘግየት ወይም ሳይፈጸም መቅረት ነው። እግዚ
አብሔር ይባርከናል ብለው ጠብቀዋል፤ እየሆነ ያለው ግን ተቃራኒው
ነው። ለኑሮ ስኬት እርሱን ተስፋ አድርገዋል፤ በአብዛኛው ሲሆን የሚታ
የው ግን ሌላ ነው። ስለዚህ በእግዚአብሔር ተስፋ ቆርጠዋል። በእርግጥ
በሚዘገይ ተስፋ የልብ ሐዘን መኖሩን መጽሐፍ ቅዱስም ይነግረናል
(ምሳ. 13÷12)። የእኔ ጥያቄ ግን መጀመሪያውኑ እየጠበቅን ያለነው እግ
ዚአብሔር የሰጠንን ተስፋ ነው ወይ? የሚል ነው።

አንዳንዴ እግዚአብሔር ያልተናገረንን ቃልና ያልሰጠንን ተስፋ
ይዘን ነው የምንጠብቀው። እግዚአብሔር የተናገረንን ሳይሆን፣ በልባችን
የተመኘነውን ነው “እግዚአብሔር የሰጠኝ ተስፋ!” ብለን የምንይዘው።
እርሱ ደግሞ ያልሰጠውን ተስፋ የመፈጸም ግዴታ ስለሌለበት፣ ነገሩ



ሳይሳካ ሲቀር እንብረከረካለን፤ እንዝላለን። እስቲ አንድ መጽሐፍ ቅዱ
ሳዊ የተስፋ ቃል ላስታውሳችሁ፤ “ለእናንተ የማስባትን ሐሳብ እኔ ዐው
ቃለሁ፤ ፍጻሜና ተስፋ እሰጣችሁ ዘንድ የሰላም ሐሳብ ነው እንጂ የክፉ
ነገር አይደለም” (ኤር. 29÷11)። ቆይ፣ “አሜን” ለማለት አትቸኩሉ።
ይህንን ቃል ሰባኪዎች ብዙ ጊዜ ይሰብኩታል፤ ለትንቢት ተናጋሪዎችማ
የትንቢታቸው አዝማች ነው። እኛም እንዲህ ዐይነት ተስፋ ልባችንን
ያሞቀዋል፤ ለዚህ ሳይሆን አይቀርም ይህ ጥቅስ በበርካቶች ቤት ግድግዳ
ላይ በተለያየ መልኩ ተሰቅሎ የሚታየው። ነገር ግን ሁሉም ሰው ትክክ
ለኛውን ሐሳብ ሳይሆን፣ በልቡ የሚያስበውንና ደስ የሚያሰኘውን ትር
ጓሜ ነው ለዚህ ጥቅስ የሚሰጠው።

ይህ ቃል የተነገረው እስራኤላውያን በባቢሎን ምርኮ ሳሉ ነው።
እስራኤላውያን ወደ ባቢሎን የተወሰዱት በተለያየ ጊዜ መሆኑ ይታወ
ቃል። የተወሰኑት በባቢሎን፣ ሌሎቹ ደግሞ እስራኤል ሳሉ፣ አንዳንድ
ነቢያት እግዚአብሔር የባቢሎንን ቀንበር ሰብሮ ወደ አገራቸው እንደሚ
መልሳቸው ትንቢት ይናገሩ ነበር። የእግዚአብሔር ነቢይ የሆነው ኤርም
ያስ ግን፣ ”ይህ ልክ አይደለም፤ ሰባው ዓመት እስኪሞላ በዚያው በም
ርኮ መቆየታችሁ የእግዚአብሔር ሐሳብ ነው” ለማለት ነው ይህንን መል
እክት የተናገረው።

ስለዚህ በዚያው በባቢሎን “ቤት ሠርታችሁ ተቀመጡ፤ አታክ
ልትንም ተክላችሁ ፍሬዋን ብሉ፤ ተጋቡ ወንዶችንና ሴቶች ልጆቻችሁ
ንም አጋቡ፤ እነርሱም ወንዶችንንና ሴቶችን ልጆች ይውለዱ፤ ከዚ
ያም ተባዙ” ነበር እግዚአብሔር የሚለው (ቁ. 5-6)። ይህ ነበር የእግዚአ
ብሔር ሐሳብ! በምርኮ ምድር ተረጋግተው እንዲኖሩ፣ ሰባው ዓመት ካላ
ለቀ አይወጧትምና ያለ ምንም ዐመፅ ከአሕዛብ ቀንበር በታች እየተገዙ
እየተባዙ እንዲኖሩ ማስጠንቀቅ!

በእርግጥ እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የሰጠው ፍጻሜና ተስፋ
ያለው ሐሳብ በባቢሎን በምርኮ ምድር ለዘላለም እንዲኖሩ አይደለም።
እስከዚያው ግን እዚያው መቆየታቸው አይቀርም። እንዲያውም፣ ለባቢ
ሎን እንደዲጸልዩም ታዘዋል። “በእርሷ ሰላም ሰላም ይሆንላችኋልና ወደ
እርሷ ላስማረክኋችሁ ከተማ ሰላምን ፈልጉ፤ ስለ እርሷም ወደ እግዚአብ
ሔር ጸልዩ” (ቁ. 7)። ለመሆኑ ስንቶቻችን ስለ ሶማሊያና ስለ ኤርትራ
እንጸልያለን? ብዙዎች ይህንን ኀላፊነት እንደ ዘነጋን ነጋሪ የሚያስፈልግ
አይመስለኝም። እግዚአብሔር ግን ሰላም የምታገኙት ጠላታችሁ የሆነ
ችው፣ የማረከቻችሁ፣ የምታሠቃያችሁና የጕን ውጋት የሆነችባችሁ
ከተማ (አገር) ሰላም ሲኖራት በመሆኑ ሰላም እንዲኖራት ጸልዩ ነው ያላ
ቸው። አስተውሉ! ጸልዩባት ሳይሆን፣ ሰላም እንድታገኝ ጸልዩላት ነው
ትእዛዙ፤ አቤት የእግዚአብሔር ልብ!

ታዲያ ይህንን ቃል ምን ዐይነት ተስፋ አድርጋችሁ ነው የምታስ
ቡት? “በምርኮ ቆዩ” የሚል ተስፋ?! እስቲ ልብ ካላችሁ አሁን “አሜን”

በሉ! ዝም ብሉ በደፈናው እግዚአብሔር፣ "ስአንተ የማስባት ሐሳብ መልካም ነው" ብሎኛል በማለት ትርጓሜውን ሳያጤኑ መጣደፍ አያስኬድም። እግዚአብሔር ያላሰንን ነገር በራሳችን ግንዛቤና መረዳት እርሱ እንደ ሰጠን ተስፋ አድርጐ መውሰዱ ችግር ውስጥ ነው የሚከትተን። ጌታ ሲናገር ጫፍ ይዞ በስሜት መወራጨት አይጠቅምም። ነገ የልብ ስብራት ነው ትርፉ።

ጌታ ኢየሱስ ከሙታን ከተነሣ በኋላ ሐዋርያው ጴጥሮስ በሞቱ እንዴት ጌታን እንደሚያከብር አስቀድሞ ተናገረው (ተስፋ ሰጠው)። በዚያን ወቅት ጴጥሮስ ዘወር ሲል ዮሐንስን አየና የዮሐንስንም የነገ ዕጣ ለማወቅ በመጓጓት፣ "ጌታ ሆይ ይህስ (ዮሐንስ) እንዴት ይሆናል?" ብሎ ጠየቀ። ኢየሱስም፣ "እስከመጣ ድረስ ይኖር ዘንድ ብወድስ ምን አግዶህ? አንተ ተከተለኝ" ብሎ መለሰለት። ይህችን ጫፍ የያዙ ሐዋርያት ግን፣ "ያ ደቀ መዝሙር አይሞትም" ብለው አስወሩ። ጌታ ግን፣ "እስከመጣ ድረስ ይኖር ዘንድ ብወድስ፣ አንተን ምን አሳሰበህ?" አለው እንጂ አይሞትም አላለውም። ካላመናችሁኝ ክፍሉን አንብቡ (ዮሐ. 21፥21-23)። ደግነቱ የዚህ መልእክት ባለጉዳይ የሆነው ዮሐንስ ትክክለኛው የኢየሱስ ምላሽ ገብቶት ነበር እንጂ ዮሐንስ ሲሞት፣ "ጌታ 'አትሞትም' ብሎት እንዴት ይሞታል?" በማለት ብዙዎች በተሰናከሉ ነበር። እነ ጴጥሮስ ጌታ ምንድን ነው በትክክል የተናገረው? ምን ለማለት ነው የፈለገው? ብለው መመርመር አልፈለጉም፤ እኛም ዛሬ እንዲሁ ነን።

በጣም በጠና ታምማ በሞት አፋፍ እያለች፣ "አከብርሻለሁ" የሚል መልእክት ተነግሮአት፣ በዙሪያዋ ያሉት ወገኖች "ጌታ ድል ባለ ድግስ ሊድራት ነው" ብለው ሲጠብቁ፣ እርሱ ግን ወደ ራሱ ስለ ሰበሰባት እኅት መስማቴ ትዝ ይለኛል። ብዙዎች ደነገጡ፤ እምነታቸውም ተናወጠ። ግን እስቲ "አከብርሻለሁ" ማለት "አድርሻለሁ" ማለት ነው ብሎ የወሰነው ማነው? አያችሁ ልጆች፣ እርሱ የሚለውና እኛ የምንሰጠው ትርጉም ምን ያህል እንደሚራራቅ! ጌታ ስለ ስኬት ተናግሮን፣ ስለ በረከት ተስፋ ሰጥቶን ሊሆን ይችላል፤ ታዲያ ስኬት ሁሌ ከገንዘብ ጋር የግድ መያያዝ አለበትን? በእግዚአብሔር ትርጓሜ፣ ስኬት ማለት "በእግዚአብሔር ፈቃድ መኖር" ይመስለኛል። በእኛ ደግሞ ዝናና ገንዘብ በአጠቃላይም አዱኛ ማለት ሆኖአል። "አባርካችኋለሁ" ካለን ደግሞ በዐይናችን ፊት ደምቆ የሚታየን ገንዘብ ወይም የኑሮ ከፍታ ነው። ስለ ዚህ ገንዘብ ሳይሰጠን ሲቀር ሌላ በረከት ብናገኝም እናዝንበታለን። በረከት ማለት የግድ ገንዘብ ማለት ከሆነ አነሙስጠፋ ተባርከዋላ?!

ሰዎች ተመሳሳይ ቋንቋ ስለ ተነጋገሩ ሁልጊዜ ይግባባሉ ማለት አይደለም። አንዳንዴ ከሰዎች ጋር በአንድ ቋንቋ እየተነጋገርኩ መግባባት ሲሳነን፣ "አማርኛ ላለመግባባትም ያገለግላል ለካ!" የምልባቸው ወቅቶች አሉ። ዐዋጅ ሲወጣ ነጋሪት ጋዜጣ ላይ እንደሚታየው፣ መጀመሪያ



"እንዲህ ማለት እንዲህ ማለት ነው" በማለት የቃላት ትርጉም የሚዘረዘረው ለዚህ ሳይሆን አይቀርም። የጋራ መግባባት እንዲፈጠር በቃላት ትርጓሜ መስማማት የግድ ይላል።

ሌላ ጉዳይም አለ። ክርስቲያን ከሆናችሁ ችግር ብሎ ነገር፣ እንኳን ሊያገኛችሁ በአጠገባችሁ ዝር አይልም ብሎ እግዚአብሔር የት እንደተናገረ ባላውቅም፣ ትንሽዬ ችግር ገና በአካባቢያቸው ሲያልፍ የሚበረግጉና የእግዚአብሔርን ከእነርሱ ጋር መኖር የሚጠራጠሩ የዋህ ክርስቲያኖች ጥቂት አይደሉም።

ሮናልድ ደን እንዲህ ይላሉ፤ "ከምወዳቸው የብሉይ ኪዳን ሰዎች መካከል ጌዴዎን አንዱ ነው። በመሳፍንት 6 ውስጥ እስራኤል ከምድያማውያን የባርነት ቀንበር በታች ስትሠቃይ እናገኛታለን። ጌዴዎን በወይን መጥመቂያ ውስጥ ስንዴ እየወቃና ይህንንም ከምድያማውያን እየደበቀ ነበር። በድንገት አንድ መልአክ በእቅራቢያው ከሚገኝ ዛፍ ሥር ተቀምጦ፣ ጌዴዎንን 'አንተ ጽኑዕ ኃያል ሰው፤ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነው' ብሎ ተናገረው (መሳ. 6፥12)።

"መልአኩ በድንገት ሲናገር ጌዴዎን ምናልባት በድንጋጤ ወደ ላይ ዘልሎ ሊሆን ይችላል። መልአኩ፣ 'ጽኑዕ ኃያል' ብሎ ሲጠራውም ነገሩ ትንሽ የተጋነነ መስሎት ይሆናል። ለመልአኩ ሰላምታ፣ ጌዴዎን ምን ብሎ እንደ መለሰ ታስታውሳላችሁ? 'ጌታዬ ሆይ፤ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ይህ ነገር ሁሉ ለምን ደረሰብን? አባቶቻችንስ ... ይነግሩን የነበረ ታምራቱ ወዴት አለ? አሁን ግን እግዚአብሔር ትቶናል፤ በምድያማውያንም እጅ አሳልፎ ሰጥቶናል' (መሳ. 6፥13)።

"'እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ፣ ምንም ክፉ ነገር ሊከሰትብን አይችልም' የሚል ትምህርት ዛሬም አለ። ራሳችንን ለክርስቶስ መስጠታችን ከእግዚአብሔር ዘንድ ልዩ እንክብካቤ እንደሚያስገኝልንና ከአደጋ ነጻ እንደምንሆን የምናስብ አንጠፋም። እውነታው ግን እግዚአብሔርን መውደድና መከተል ከችግር ነጻ የመሆን ዋስትና አለመስጠቱ ነው። 'በክርስቶስ የሚታመኑ ጭጋጋማ ቀናት አያገኛቸውም' ተብሎ ተስፋ አልተገባምና በሰው የሚደርሰው ሊደርስብን ይችላል።"[1] ታዲያ መከራ ባጋጠመን ቁጥር ባልተገባልን ተስፋ እግዚአብሔርን መቀየማችን ከየት መጣ?

ይህ ችግር በተለይ በአገልጋዮች ላይ ጐልቶ ይታያል ለማለት እደፍራለሁ። እግዚአብሔር ለአገልግሎት የሚወጡበትን ራእይ ሲሰጣቸው ድሉን ብቻ ተስፋ በማድረግ መንገድ ይጀምሩና ጉድ ይሆናሉ። እንዲያውም እውነቱን እንነጋገር ከተባለ የአገልግሎት ጥሪ የመከራ ጥሪ ይመስለኛል። ሆኖም እግዚአብሔርን ካልፈሩ እንደ አገልግሎት እትራፊ ቢዝነስም የለም (ደሞዛቸውን እዚሁ በምድር ላይ መቀበልና ሒሳብ መዝጋት ለሚፈልጉ ማለቴ ነው)።

ለዚህ ነው ጥቅሙን እንጂ ለአገልግሎት የሚከፈለውን መከራ ሳያለቡና ዋጋቸውን ሳይተምኑ በእግዚአብሔር ለመነገድ በየዕለቱ ወደ ዘማች "አገልጋዮች" ለአገልግሎት የሚለማሩት:: ኤርምያስ ለአገልግሎት በተጠራበት ጊዜ እግዚአብሔር የሰጠው ተስፋ፣ "እነሆ ቃሌን በአፍህ ውስጥ አኑሬያለሁ፤ እነሆ ትነቅልና ታፈርስ ዘንድ፣ ታጠፋና ትገለብጥ ዘንድ፣ ትሠራና ትተክል ዘንድ በአሕዛብና በመንግሥታት ላይ ዛሬ አድርጌሃለሁ" የሚል ነበር (ኤር. 1፥10):: ታዲያ በመንግሥታት ላይ የተሾመ አገልጋይ መከራ እንዳለበት መጠበቅ የለበትም? ሹመት (ኀላፊነት) እና መከራ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸዋ! በዘመናችን በታላቅ የፈውስ ኀይል እግዚአብሔርን እያገለገለ ያለው ቤኒ ሂን፣ "ከትልቅ ቅባት ጋር ትልቅ መከራ መኖሩ ቀደም ብሎ ገብቶኝ ቢሆን ኖሮ ቅባቱን አልፈልገውም ነበር" ማለቱ ሲነገር ሰምቻለሁ:: ዐውቃችሁ ግቡበት ነው ነገሩ!

እናላችሁ ኤርምያስ ትንቢት ይናገራል፤ ይደበድቡታል፤ ያገለግላል ግን ይራባል:: የእግዚአብሔርን ቃል ያመጣል፤ ወደ ግዞት ይጥሉታል:: አገልግሎት ማለት መከራ መሆኑ ያኔ በሂደት እየገባው መጣ፤ "በእውነትም በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ" መባሉን ታውቁ የለ? (2ጢሞ. 3፥12):: መስቀል ማለት ይህ አይደል እንዴ! ሐሰተኛ ነቢያት ግን በምቾት ይኖሩ ነበር እንጂ አንዳች መከራ አልነበረባቸውም:: ይህ ደግሞ ዛሬም እውነት ነው፤ ዛሬም በእግዚአብሔር ይነገዳል!

ኤርምያስም እግዚአብሔር፣ "በመንግሥታት ላይ ሾሜሃለሁ" ሲለው ለካ ስለ በረከትና ስለ ምቾት አያወራ እንዳልነበር ሲገባው ደነገጠ፤ መሸወዱ ገባው:: ለዚህ ነው "አቤቱ አታለልኸኝ፥ እኔም ተታለልሁ" ያለው (ኤር. 20፥7):: "ኧረ ኤርሚያስ እንዲህ አይልም፤ ይህማ የእግዚአብሔር ቃል አይመስልም!" ብላችሁ አሰባችሁ አይደል? ግድ የለም ብሏል፤ እናንተም አኮ አፍ አውጥታችሁ ባትናገሩም ይሄኔ በልባችሁ እያላችሁት ሲሆን ይችላል:: እኔም ልክ እንዲሁ የማስብበት ወቅት ነበር:: "እግዚአብሔር ሆይ ስትጠራኝ የነገርከኝን ተስፋ ሳስብ አዱኛ፣ ዝና፣ ክብር፣ ብልጽግናና ሲሳይ ነበር የታየኝ:: በራሴ መረዳት ነበር የተረጐምኩት፤ ለካ ሸውደኸኛል:: በእውነትም ደግሞ ተሸውጃለሁ" ማለት ነው የፈለገው::

ወዳጆቼ ሆይ፤ እናንተም እግዚአብሔር ያልሰጣችሁን ተስፋ አትጠብቁ:: መጀመሪያ እግዚአብሔር ሲናገራችሁ በትክክል ምን ማለት እንደፈለገ ተረዱ:: በንግግር መግባባት እንዲኖር የቃላት ትርጓሜያችን መጣጣም እንዳለበት ተግባባን አይደል? "እነሆ በቶሎ እመጣለሁ" (ራእይ 22፥12) ካለን አኮ ሁለት ሺህ ዓመት ሆነው! በእርሱ አነጋገር "ቶሎ" ማለት እስከ ሁለት ሺ ዓመት የሚደርስ የጊዜ ክልልን የሚያጠቃልል አባባል ሊሆን ይችላል:: "አባርካችኋለሁ" ሲልስ ምን ማለቱ ይሆን? ከአባቱ ቤት ባዶ እጁን የወጣው ያዕቆብ ያን ሁሉ ልጅ፣ ንብረት እና ከብት እስከትሎ ሳለ፣ እግዚአብሔር ሲታገለው "ካልባረክኸኝ አልለቅህም" ማለቱ በረከት የግድ ከንብረት ጋር ብቻ ላይያያዝ እንደሚችል አይጠቁመን ይሆን? ስለ ስኬት ሲናገረንስ ምኑ እያሰበ ነው? አገልጋዮችም በመጀመሪያ መጨረሻውን የሚያይ አምላክ ስለ አገልግሎታችሁ ጅማሬና ፍጻሜ ሲገልጥላችሁ፣ በየመሐሉ ምን ሊያጋጥማችሁ እንደሚችል አስተውሉ:: ልባችሁንም ጠብቁ::



ማስታወሻ

[1] Ronald Dunn, *Don't Just Sit There ... Have Faith* (England, Alpha Books) pp.114-115.

## ባልጸልይስ?

ነጋዴው ሸቀጣ ሸቀጡን በበርካታ ግመሎች ላይ ጭኖ እያግተለተለ በረሃውን አቋርጦ በቱርክ አርሜንያ ውስጥ ወደምትገኝ አንዲት ከተማ መጓዝ ጀመረ። ይህ አርመናዊ ነጋዴ ወላጆቹ ክርስቲያኖች ስለነበሩ በክርስቲያናዊ አስተዳደግ ያደገ በመሆኑ በየዕለቱ በጸሎት ራሱን ለእግዚአብሔር አሳልፎ መስጠትን የሕይወቱ ልማድ አድርጐታል።

ይህ ታሪክ በተፈጸመበት ወቅት፣ አገሪቱ ከአንድ ከተማ ወደ ሌላ ሩቅ ከተማ የሚጓዙ ነጋዴዎችን በመዝረፍ በሚተዳደሩ የኩርድ ሽፍቶች ተወርራ ነበር። ነጋዴው ባያውቅም፣ እነዚህ ሽፍቶች ማታ ለዐዳር በሚያርፍበት የመጀመሪያ ስፍራ ሲዘርፉት አስበው በርቀት እየተከታተሉት በመጓዝ ላይ ነበሩ።

ልክ የመረጡት ሰዓት ሲቃረብ፣ ነጋዴው ምሽቱን ለማሳለፍ ወዳረፈበት ስፍራ ጨለማውን ተገን አድርገው ተጠጉ። በሚያስገርም ሁኔታ አካባቢው ጸጥ ረጭ ብሏል። ምንም ዐይነት ጠባቂዎችና ቃፊሮች አልነበሩም። ስለዚህም በጣም የልብ ልብ እየተሰማቸው በጣም ሲጠጉ ግን እጅግ ረጃጅም ቅጥሮች በቦታው መኖራቸውን ተገነዘቡ፤ በዚያ ቦታ ከዚህ በፊት ምንም ዐይነት ቅጥር አለመኖሩን ያውቃሉና ተደንቀዋል።

በማግስቱም ይህንኑ ነጋዴ ተከትለው ሲጓዙ ቢውሉም ማታ ግን እነዚያ የማይታለፉ ግንቦች አጋጠሚቸው። በሦስተኛው ሌሊትም ያው ነው፤ ቅጥሮቹ አሉ። ሆኖም በቅጥሮቹ ዙሪያ ትናንሽ ንድባዎች ስለነበሩ በእነዚያ ሾልከው ገቡ።

የሽፍቶቹ አለቃ ይህ ምስጢራዊ ጉዳይ እጅግ አስፈርቶት ስለነበር አስቀድሞ ነጋዴውን ከእንቅልፉ ቀሰቀሰው።

"ይሄ ነገር ምንድን ነው?" በማለት ጠየቀው። "ልንዘርፍህ አስበን ከተነሣህበት ከተማ ጀምሮ ስንከታተልህ ነበር። በመጀመሪያውና በሁለተኛው ሌሊት ዕረፍት ስታደርግ በአንተና በጓዝህ ዙሪያ ረጃጅም ቅጥሮች ነበሩ፤ ዛሬ ማታ ግን ቅጥሩ ክፍተት ስለ ነበረው በዚያ በኩል ሾልከን ነው የገባነው። የዚህን ሁሉ ምስጢር ከነገርከኝ ምንም ጉዳት አናደርስብህም፤ ማንም ጫፍህን አይነካህም!"

ራሱ ነጋዴውም ነገሩ ቢያስደንቀውም እንቆቅልሽ ሆኖበታል። "ወዳጆቼ ሆይ!" ብሎ ጀመረ፤ "በዙሪያችን ቅጥሮች እንዲኖሩ ብዬ አንድም ያደረግሁት ነገር የለም። እኔንና አብረውኝ ያሉትን ሁሉ ለእግዚአብሔር ለማስረከብ በየቀኑ ማታ ማታ እንደምጸልይ ብቻ ነው የማውቀው። እግዚአብሔር ከክፉ ሁሉ እንደሚጠብቀኝ ከልቤ አምናለሁ፤ ዛሬ



ማታ ግን በጣም ስለ ደከመኝና እንቅልፍ ስለ ተጫጫነኝ ምን እንደጸለይኩ እንኳን በቅጡ አላስታውስም። እናንተ ጥሰችሁ መግባት የቻላችሁት በዚህ ምክንያት መሆን አለበት!" አላቸው።

ኩርዳውያኑ በዚህ ምስክርነት ልባቸው ተሸነፈ። ስለዚህ በዚያው ስፍራ ኢየሱስ ክርስቶስን ለመከተል ወሰኑ። ዘራፊና ሽፍታ የነበሩት የእግዚአብሔር ሰዎች ሆኑ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ግን አርመናዊው በጸሎት ቅጥሩ ላይ የተፈጠረውን ክፍተት በፍጹም አይረሳውም።

በአጋጣሚ ብቻ ከሚደረግ ግዴለሽ ጸሎቱ ይልቅ በየዕለቱ በሚደረግ ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር በየዕለቱ መገናኘት ምን ያህል ኀይል እንዳለው የዚህ አርመናዊ ክርስቲያን ነጋዴ ታሪክ ያስረዳናል።

ይህንን ታሪክ የተናገሩት በኀይለኛ የምልጃ ጸሎታቸው የሚታወቁት ጉርደን ሲንድሴይ ናቸው፤ "Prayer That Moves Mountains" (ተራሮችን የሚያንቀሳቅስ ጸሎት) በሚለው መጽሐፋቸው።[1]

ስለ ጸሎት ሲነሣ የማርቲን ሉተር አባባል ሁሌ ትዝ ይለኛል፤ "ዛሬ ብዙ ሥራ ስላለብኝ የመጀመሪያዎቹን ሦስት ሰዓታት በጸሎት ማሳለፍ አለብኝ" ነበር ያለው። በርካቶች ሥራ ከበዛባቸው ጸሎትን ቸል ይላሉ - ጸሎት ሥራ ፈትነት ይመስል! ጸሎት ግን ትልቅ ሥራ ነው።

አንድ ጊዜ ሮናልድ ደን እንዲህ አሉ፤ "የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን በጸሎት ርእስ ላይ ሳስተምር ቆይቼ ስጨርስ የአንድ ቤተ ክርስቲያን መሪ ወደ እኔ መጥቶ ትከሻዬን መታ መታ አደረገኝና 'ይህ የጸሎት ጉዳይ በጣም ትልቅ ሐሳብ ነው፤ ግን ከቁጥጥር ውጭ እንዳይሆን እፈልጋለሁ' አለኝ።

'ምን ማለትህ ነው?'

'ሰዎች በጣም በጸሎት ከመጠመዳቸው የተነሣ ምንም ሥራ ሳይሠሩ ይቀራሉ።'

የሚገርማችሁ፣ 'ሌላ ሥራ' አላለኝም፤ 'ምንም ሥራ' ነው ያለኝ። ሰውዬው የሚናገረው ከልቡ እንደሆነ ስረዳ፣ በጣም ከመጸለያቸው የተነሣ ቀዝቀዝ እንዲሉ የተነገራቸው አብያተ ክርስቲያናት እስካሁን አጋጥመውኝ እንደማያውቅ ነገርኩት" ብለዋል።[2]

በመሠረቱ ጸሎት የሥራ ምትክ ወይም የሥራ ዝግጅት አይደለም። ራሱ ሥራ ነው። ስለዚህ ስንጸልይ የምንከፍለው ዋጋ ይኖራል፤ እስቲ ቀጣዩን የቤኒ ሂንን ምስክርነት እንመልከት።

1980 ዓ.ም. አንድ ቅዳሜ ምሽት፣ እኩለ ሌሊት ነው። በሚቀጥለው ቀን ማለዳና ምሽት፣ ከከተማው ወጣ ባለ አንድ ቤተ ክርስቲያን አገ

ልግሎት ስላለኝ ባረፍኩበት ሆቴል መኝታ ክፍሌ ውስጥ በጸጥታ እየጸለኩና ጌታን እያመለክሁ ነው።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ የእግዚአብሔር መገኘት (ሀልዎት) በነበርኩበት ክፍል በኃይል ስለ ተገለጠ እንባ በጉንጮቼ መውረድ ጀመረ፤ ክብሩ ከበበኝ። የእግዚአብሔር ሀልዎት ብርቱ ነበረና በዙሪያዬ ያለውን ነገር ሁሉ ረሳሁ። ምኑንም ሳላውቀው ከምሽቱ 8:00 ሰዓት ሆኗል፤ እኔ ግን ገና እየጸለይኩ ነበር። በተከታዩ ማለዳ መነቃቃትና ብርታት እየተሰማኝ በፍጥነት ከመኝታዬ ወረድሁና ወደ አገልግሎት ከመሄዴ በፊት እንደገና መጸለይ ጀመርኩ። በዚህ ጊዜ ግን የጸሎት ጊዜዬ ልዩ አልነበረም። እንደ ትላንትናው ምሽት ዐይነት ስሜትም አልተሰማኝም። ከዚያ ወደ አገልግሎቱ ሄድኩና ሰዓቱ እንደደረሰ ስብከቴን ጀመርኩ። የመጀመሪያዎቹን ቃላት ለመናገር አፌን ስከፍት ያኔ ሕንጻው በክብሩ ደመና ተሞላ። እጅግ ኃያሉ አምላክ በቅዱስና አስፈሪ በሆነው ሀልዎቱ የመጣ ነበር የሚመስለው። የተገለጠው ክብር መንቀሳቀስ እስኪያቅት ድረስ እጅግ ኃይለኛ ነበር። ሰዎች ማልቀስ ጀመሩ። እየተናገርኩ ሳለ፣ አንዳንዶች ከመቀመጫቸው ላይ ወደ መሬት እየወደቁ፣ እየተንከባለሉ ያለቅሳሉ። ምላሻቸው አስደናቂ ነበር።

ከዚያ ዐይኖቼን ጨፈንኩና አንድ ቃል ተናገርኩ - "ኢየሱስ!" አቤት! የእግዚአብሔር ሀልዎትና ኃይል ከፊት ይልቅ የጉባኤ አዳራሹን ሞላውና በየስፍራው ሁሉ ሰዎች ተነክተው መንቀሳቀስ ጀመሩ። በሚታይ ሁኔታ ያልተነካ አንድ ሰው አልነበረም።

አጠገቤ ያለው ሰው፣ "የእግዚአብሔር መገኘት አሁን እየተሰማኝ ያለውን ያህል በፍጹም ተሰምቶኝ አያውቅም" ብሎ ተናገረኝ። እንባ በጉንጮቹ ይወርዳል።

እውነቱን እንደ ነበር ዐውቃለሁ። እኔም ብሆን ከዚህ በፊት የመንፈስ ቅዱስ መገኘትና ቅባት በዚያን ያህል ኃይል በየትኛውም አገልግሎት አጋጥሞኝ አያውቅም።

ከአገልግሎቱ በኋላ ዲትሮይት ከተማ ውስጥ ከምትኖር የአክስቴ ልጅ ዘንድ ምሳ እንደምበላ ፕሮግራም ተይዞልኛል። ለረጅም ጊዜ ስላልተገናኘንም ከእርሷ ጋር ምሳ መብላትን በናፍቆት ነበር የምጠብቀው።

የአክስቴ ልጅና ባለቤቷም ቤታቸው ስደርስ በጥሩ ሁኔታ ተቀበሉኝ። አብረን ተቀምጠንም መጫወትና ትዝታችንን ማደስ ጀመርን። ምሳው በጣም አስደሳች፣ ጨዋታችንም የተነቃቃና ሣቅ የሞላበት ነበር። ምሳውን እየተመገብን ሳለ ጌታ በድንገት በልቤ መንቀሳቀስ ጀመረ፤ ስሜቱን በደንብ ዐውቀዋለሁ። "ሂድና ጸልይ" ነበር የሚለኝ።

ደነገጥኩና "ጌታ ሆይ፤ አሁን መነሣት አልችልም። ከእነዚህ ሰዎች ጋር ምሳ ላይ ነኝ። በዚህ ላይ ደግሞ እዚህ እንኳ ያደረሱኝ



ምሳችን አበቃ፤ እዚያ ያመጣኝ ሰው ወደ ሆቴል ክፍሌ በመኪና መልሶ አደረሰኝ። ክፍሌ ስደርስ እጅግ ከመድከሜ የተነሣ ትንሽ ጋደም አልኩ።

ወደ ምሽት አገልግሎት ስፍራዬ ስደርስ የጠዋቱን ዕጥፍ የሚያህል ሕዝብ ተሰብስቧል። ጠዋት የነበረው የእግዚአብሔር ኃይል እጅግ አስፈሪ ከመሆኑ የተነሣ ሕዝቡ አሁንም ድረስ የዛሬ ማታውን አገልግሎት በደስታና በጉጉት ተሞልቶ ይጠብቃል። የጠዋቱ ጉባኤ ያን ያህል ኃይለኛ ከነበረ የማታው እንዴት ይሆን ይሆን?

ልሰብክ ተነሣሁ፤ ሆኖም አፌን ስከፍት ምንም አልነበረም - ባዶ ቃላት ብቻ። የእግዚአብሔር ሀልዎት የለም። የመንፈስ ቅዱስ ቅባት የለም። ኃይል የለም።

ታገልሁ፤ ቀጥዬ ምን ማድረግ እንዳለብኝም አላወቅሁም። ምን እየሆነ እንዳለ ብዙዎች በመገረም ላይ እንደሆኑ የፊታቸው ገጽታ ያስታውቃል። እውነቱ ግን ምንም እየተካሄደ አለመሆኑ ነበር።

ከጥቂት ሰዓታት በፊት "ኢየሱስ" የሚለውን ቃል ብቻ ተናግሬ የእግዚአብሔር ኃይል የተሰበሰብንበትን አዳራሽ ሞልቶት ነበር። ሕዝቡ በእግዚአብሔር ተነክተው በእግዚአብሔር ሀልዎት ውስጥ ያለቅሱ ነበር። አሁን ግን ማሰብ የቻልኩትን ያህል የተለያዩ ነገሮችን እየተናገርኩ እንኳ ምንም እየተከናወነ አይደለም።

በመጨረሻ ፕሮግራሙ አለቀ። ኪሳራ ነበር! ወደ ሆቴል ክፍሌ ለመድረስ ተጣደፍኩ። እንደ ደረስኩም ወደ ክፍሌ ገባሁና በሩን ቆለፍኩት። ኡፍ ግልግል! ፕሮግራሙ አላልቅ ብሎኝ ነበር።

መኝታዬ ላይ ቁጭ ስል አእምሮዬ ያንን የሥቃይ ጊዜ ማሰብ ጀመረ። እንቆቅልሽ ሆኖብኝ ግራ ተጋብቻለሁ። "እግዚአብሔር ሆይ ምንድን ነው የሆነው? ዛሬ ጠዋት ሀልዎትህ በጣም በኃይል ከመገለጡ የተነሣ በክብርህ መሐል መቆም ሁሉ አቅቶኝ ነበር። ሕዝቡም በእንባ ተሞልቶ ነበር።" ቃላቱ ከእኔ መውጣታቸውን ቀጠሉ፤ "ልክ መንግሥተ ሰማያት ነበር'ኮ የሚመስለው። ለመሆኑ ችግሩ ምንድን ነው? ፕሮግራሙ ለምን ሕይወት አልባ ሆነ? ለምን አንተ የሌለህበት ሆነ?" በመጨረሻ አቆምኩ። ያ እርግት ያለውና ለስላሳው የመንፈስ ቅዱስ ድምፅ፣ "'ሂድና ጸልይ' እያልኩ ዛሬ ከሰዓት በኋላ እጐተጉትህ እንደነበረ ታስታውሳለህ? አንተ ግን ከአክስትህ ልጅ ጋር መቆየትን መርጠሃል። ለእኔ የተገባኝን ስፍራ ለአክስትህ ልጅና ለባለቤቷ ሰጠሃቸው። እነርሱን ከእኔ አስቀደምክ!" አለኝ።

በጣም ረጋ ብዬ፣ "ግን'ኮ ጌታ ሆይ፤ ትቼ መውጣት አልችልም ነበር። የአክስቴ ልጅ ምን ትለኛለች?" በማለት ራሴን ለመከላከል ምላሽ ሰጠሁ።

ድምፁ አሁንም ለስላሳና ጨዋ ነበር። "ያ የምትከፍለው ዋጋ አካል ነው። ቤን ሂን፣ ለቅባቱ ዋጋ ለመክፈል ፈቃደኛ ነህ?"

ቁልፉ ይህ ነው ከኢየሱስ ጋር መሆን - አሁንም አሁንም፤ በቋሚነት፤ በቀን ለጥቂት ደቂቃና ወቅት እየጠበቁ አይደለም። ያኔ ቅዳሜ ማታ ከኢየሱስ ጋር ነበርሁ። በኋላ ሲፈልገኝ ግን ብቻዬን ተለይቼ አብሬው ለመሆን ፈቃደኛ አልሆንኩለትም።[3]

ከላይ ያነበብነው ታሪክ ከጌታ ጋር በጸሎት ስለ መቆየት ብዙ የሚያስተምረን እንዳለው አስባለሁ። ለአገልግሎታችን ጸሎት መሠረታዊ ነገር ነው። ሳይጸልዩ ፍሬያማ አገልግሎትን መመኘት፣ "ላም ባልዋለበት ..." ዐይነት ይሆናል። ሮናልድ ደን ይቀጥላሉ፤ "ሰይጣን የጸሎትን መሣሪያ የሚከላከልበት ዐቅም የለውም። የፀረ ጸሎት ሚሳይል የለውም። ለምሳሌ፣ አንድ ያሳመነ ሰው የወንጌል ስርጭት ዘመቻችንን የሚቃወምበት በርካታ መከላከያዎች አሉት። ቤተ ክርስቲያን አልመጣም ሊል ይችላል፤ በአጋጣሚ ቢመጣም ኮርኒስ ሲቆጥር ውሎ ሊመለስ ይችላል። ወደ ቤቱ ልትሄዱ ትችላላችሁ፤ ግን አላስገባም ይላችኋል። መንገድ ላይ ትራክት ትሰጡታላችሁ፤ ሊወረውረው ይችላል። ስልክ ደውሉለት፤ ጆሮአችሁ ላይ ይዘጋዋል። ነገር ግን ከምልጃ ጸሎታችን የተነሣ ኢየሱስ የልቡን በር እንዳያንኳኳ መከልከል አይችልም። በሌላ በምንም መንገድ ልንደርሳቸው የማንችላቸውን ሰዎች በጸጋው ዙፋን በኩል በጸሎት ልንደርሳቸው እንችላለን።"[4]

ጸሎት ሥራ ነው ብለናል። የሚገርመው ደግሞ እኛንም የሚቀርጽና የሚሠራ መሆኑ ነው። የሰውን የጸሎት ሕይወት ካወቅን ሰውየውን ዐወቅነው ማለት ነው። የትኛውም ክርስቲያን ከጸሎት ሕይወቱ አይበልጥም፤ የጸሎት ሕይወቱም ከግላዊ ሕይወቱ መብለጥ አይችልም። ልዕለ ቅዱሳንና የቅድስና ጀግኖች መሆን አለብን ማለቴ አይደለም፤ ኑሮአችንን ከጸሎታችን መነጠል አንችልም ማለቴ እንጂ። ከእግዚአብሔር ጋር ሳይስማሙ መስበክ ይቻላል (እኔም አድርጌው ዐውቃለሁ)። ስብከት፣ ሰው ከሰው ጋር የሚያካሂደው ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ሳንስማማ የሰንበት ትምህርት ማስተማርም ሆነ ላልዳነ ሰው መመስከር እንችላለን፤ መዘመርም ይቻላል። እነዚህ ሁሉ ሰው ከሰው ጋር የሚያካሂዳቸው ናቸው። ጸሎት ግን የሰውና የእግዚአብሔር ግንኙነት ነው። ሁሉ ነገር በፊቱ የተገለጸና የተራቆተ ከሆነው አምላክ ጋር የሚደረግ አብሮነት ነው። እርሱን ደግሞ ልናታልለው አንችልም። ከእግዚአብሔር ጋር ለብቻችን ስንሆን የሚገለጠው ትክክለኛ ማንነታችን ነው። በሥራዋ እጅግ ኀይል የምታደርገው፣ "የጻድቅ ሰው ጸሎት" ናትና (ያዕ. 5÷16)።

መዝሙረኛውም እንዲህ ይላል፤ "በልቤስ በደልን አይቼ ብሆን፣ ጌታ አይሰማኝም ነበር።" ሐዋርያው ዮሐንስም እንዲህ ይገልጸዋል፦ "ትእዛዙንም የምንጠብቅና በፊቱ ደስ የሚያሰኘውን የምናደርግ ስለሆንን



የምንለምነውን ሁሉ ከእርሱ እናገኛለን" (1ዮሐ. 3÷22)። ጸሎት የሕይወት ንጽሕናን ብቻ ሳይሆን ጽናትንም ይጠይቃል። በሉቃስ ወንጌል 18÷1-8 ላይ የአንዲት መበለት ጽናት እግዚአብሔርን የማይፈራውንና ሰውንም የማያፍረውን አንድ ዳኛ ሲያሸንፍ እንመለከታለን። "በዳኛው ውስጥ ሐዘኔታ ባይኖርም መበለቷ ዘንድ ጽናት ነበረ።

"እግዚአብሔርን የማይፈራው ዳኛ ለአንዲት መንፈሰ ጠንካራ መበለት እጅ ከሰጠ፣ እግዚአብሔርማ የራሱን ሕዝብ መንፈስ ጠንካራነት እንዴት ይበልጥ ያከብር! ያዕቆብ ከመልአክ ጋር ሲታገል የነበረበትን የብሉይ ኪዳን ታሪክ ታስታውሳላችሁ? (ዘፍ. 32÷24-32)። እዚያ ታሪክ ላይ የሆነ ነገር ግር ይለኛል። ያዕቆብ እየታገለ ያለው ከመልአክ ጋር ነው፤ መሄድ እየፈለገ በያዕቆብ ከተከለከለ መልአክ ጋር! 'ሊነጋ አቀላልቶአልና ልቀቀኝ' አለው መልአኩ። ያዕቆብም፣ 'ካልባረከኸኝ አልለቅህም!' ብሎ መለሰለት (ቁጥር 26)።

"እዚህ ጋ ነው ግር የሚለኝ፤ መሄድ እየፈለገ ከአንድ ተራ ሰው ራሱን አስለቅቆ መሄድ የማይችል መልአክ አይታችሁ ታውቃላችሁ? ያዕቆብ ጠንካራ ከመሆኑ የተነሣ መልአኩን አላፈናፍን እንዳለው ነው የምታስቡት? ያ የተጠና ፍልሚያ ነው። መልአኩ 'ልቀቀኝ' ቢልም ትንፋሹን ዝቅ አድርጎ ያዕቆብን፣ 'ግን እንዳትለቀኝ አመኛለሁ። ትንሽ ገትረህ ያዝና በረከቱን ታገኛለህ' እያለው እንደሆን አስባለሁ። ምን ያህል ጊዜ በረከቱ ጋ ደርሰን ደርሰን ጥቂት ሲቀረን እንዳቆምን ገምቱ። አብርሃም ዐሥር ጻድቃን ላይ ባይቆም ኖሮ ሰዶም አትድንም ነበርን? ልክ እንደ ያዕቆብ፣ 'ካልባረከኸኝ አልለቅህም' እያልን ብንጸልይ ቤተ ክርስቲያናችን፣ አገልግሎታችን፣ ከተማችን፣ አገራችን መንፈሳዊ መነቃቃት ማየት አይችሉምን?!"[5]

ማስታወሻ

1. Larry Lea with Judy Doyle, *Hearing Ear* :Learning To Listen To God. (Florida, Creation House, 1988) pp.134-135.
2. Ronald Dunn, *Don't Just Stand There ... Pray Something : The Incredible-Power Of Intercessory Prayer* (Nashville, Thomas Nelson Publishers) pp.17-18.
3. Benny Hinn, *The Anointing* (Ben Publishing ) pp. 11-15.
4. Ronald Dunn, *Don't Just Stand There ... Pray Something : The Incredible Power Of Intercessory Prayer* (Thomas Nelson Publishers) p.20.
5. *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ* 77-78።

# እግዚአብሔር ካልመጣ . . .

አንድ ወንድም ስለ ተስፋ ቃል ሲናገር፣ “ብዙ የተስፋ ቃሎችን ጌታ ሰጥቶኛል:: ነገር ግን የምሞተው ዛሬ ቢሆንና ይህንንም አስቀድሜ ባውቅ በመቃብሬ ላይ እንዲስበክ የምፈልገው ስብከት ‘እግዚአብሔር በቃሎቹ የታመነ ነው’ የሚል ነው:: ገና የተስፋ ቃሌን ባልወርስም እንኳ ካለፍኩበት መንገድ የተነሣ ነፍሴ እግዚአብሔርን በሚገባ ዐውቃዋለች” ብሏል::

እግዚአብሔር በቃሎቹ የታመነ ነው:: አንዳንድ ጊዜ ግን የእግዚአብሔር በእኛ ጊዜ አለመምጣትና መዘግየት ብዙዎችን አላስፈላጊ የሆነ የራሳቸውን እርምጃ እንዲራመዱ ያደርጋቸዋል:: ጌታ በተናገረን ጊዜ እግዚአብሔር የተናገረውን የሚፈጽምበትን ጊዜ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ በግምት እንወስንና ሳይሆን ሲቀር እናዝናለን:: እግዚአብሔርም የራሱ ጊዜ ስላለው በእኛ ጊዜ አይመጣ ይሆናል:: ስለዚህ እግዚአብሔር ሲዘገይ ብዙዎች ስፍራቸውን ይለቃሉ:: እስቲ “እሻራ” ከሚለው የዳዊት ጸጋዬ መጽሐፍ አንድ ግጥም እንይ፤

> “ጌታ ሆይ፤
> ቤታችን ታሟል፤
> ኑሮአችን ጤና አጥቷል፤
> ግና
> ምንም ቢያሳዝንህ
> ከቶም ባትወደው፣
> አንተ ስላልመጣህ
> እኛ ልንሄድ ነው::”¹

እግዚአብሔር “ሲዘገይ” ሰዎች ስፍራቸውን እስከ መልቀቅ ሲወስኑ ይችላሉ:: ጠብቀውት ጠብቀውት ሲጎበኛቸው ሩብ ሰዓት ሲቀር የሚሄዱም አይታጡም:: እርሱ ግን ሁሉን የሚፈጽመው በዐላማ እንጂ በግብታዊነት አይደለም:: ስለዚህ እግዚአብሔር የሚዘገይባቸውን ጥቂት ምክንያቶች እንመልከት::

## <u>1. በአንድ ድንጋይ ...</u>

እግዚአብሔር ከእኛ ጊዜ ከሚዘገይባቸው ምክንያቶች አንዱ የእኛን ችግር በማስወገድ የራሱንም ዐላማ መፈጸም ስለሚፈልግ ነው:: “በጌታ ትእዛዝ ያለ ነቀፋ እየሄዱ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ነበሩ” የተባለላቸው ካህኑ ዘካርያስና ሚስቱ ኤልሳቤጥ ለዚህ ምስክሮች ናቸው:: እነዚህ ሁለት ሌዋውያን በሰው ፊት ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔር ፊት እንኳ ጻድቃን ነበሩ:: ዛሬ የብዙዎቻችን ጽድቅ በሰው ፊት እንጂ በጌታ ፊት አይደለም:: እነዚህ ቅዱሳን በቅድስና ቢመላለሱም ልጅ የሌላቸው መሆናቸውና በዕድሜም እንዳረጁ ተነግሯል:: እነርሱ በነበሩበት ማኅበረሰብና ዘመን ደግሞ ልጅ አልባ መሆን በጣም ትልቅ ውርደት ነበር:: ስለዚህ ልጅ መውለድ በጣም ይፈልጋሉ:: እግዚአብሔርም ደግሞ ለመሲሑ መንገድን የሚጠርግ መልእክተኛ (fore-runner) ይፈልጋል::



ስለዚህ እግዚአብሔር ለእነርሱ ጥያቄ የሚሰጠው ልጅ የእርሱንም ፍላጐት የሚፈጽም እንዲሆን ይፈልግ ነበር:: እግዚአብሔር የራሱ ችግር ባይኖረውም እንኳ የእኛን ችግር በመፍታት የራሱንም ዐላማ ለመፈጸም ይዘገያል ብንል የሚከብድ አይሆንም:: እግዚአብሔር ልጁን ከሕግ በታች አድርጐ የሚልክበት የዘመን ፍጻሜ ሲደርስ ግን የዘካርያስ ያለማመን ጠንቅ አላገደውም (ሉቃ. 1÷20):: ስለዚህ ለሕዝቡ የመዳንን ዕውቀት በመስጠት የእግዚአብሔርን ፍላጐት የሚፈጽም፣ ለእነርሱም የረጅም ጊዜ መሻታቸው ምላሽ የሆነውን መጥምቁ ዮሐንስን ሰጣቸው:: ይህም ዮሐንስ የእግዚአብሔርን እና የእነርሱን ፍላጐት የሚያሟላ ሆነ (ሉቃ. 1÷76-79):: ጌታ ከሚዘገይባቸው ምክንያቶች አንዱ ይህ ነው:: የእንዱን ችግር በመፍታት የራሱንም ፍላጐት ሲፈጽምበት ዘግይቶ ሲሆን ይችላል:: የእኛ ችግር የእግዚአብሔር ፍላጐት መፈጸሚያ ከሆነ መልካም ነው:: “በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ” አትሉም?

## <u>2. ምልክት እንድንሆን</u>

እግዚአብሔር የሚዘገይበት ሌላኛው ምክንያት ደግሞ በእምነታቸው ለዛሉት ምልክትና ተአምራት ሲያደርገን (ኢሳ. 8÷18) ማሰቡ ነው:: ለዚህም ምሳሌው እነዚያው ዘካርያስና ኤልሳቤጥ ናቸው:: ቅድስት ማርያም መሲሑን እንደምትፀንስ በተነገራት ጊዜ ጥያቄዋ፣ “ወንድ ስለ ማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል?” የሚል ነበር:: ለዮሴፍ የታጨች ስለ ነበረች መልእክቱ ግራ የሚያጋባ ሆኖባታል:: በድንግልና ተገኝታለች፤ ሆኖም ከዕድሜዋ ልጅነትና በዚያን ጊዜ ከነበረው የጾታ ተጽዕኖም የተነሣ በምኩራብ የሚሰጠውን የሕግ ትምህርት ለመከታተል አትችልም:: ስለዚህ እምነት የሚገኝበት ቃል ባይኖራትም ወዲያውኑ ለማመን እንደ ካህኑ ዘካርያስ ዲዳ አላስደረጋትም:: የእግዚአብሔር አገልጋይ (ካህን) ከነበረው ዘካርያስና ከድንግል ማርያም የሚጠበቀው እምነት በተሰጣቸው መጠን ነበረ እንጂ ያልተሰጣቸው አይጠበቅባቸውም:: ይህ ዛሬም እግዚአብሔር የሚጠቀምበት አሠራር ነው::

“ይህ እንዴት ይሆናል?” ለሚለው የብፅዕት ማርያም ጥያቄ መልአኩ ገብርኤል የሰጣት ምሳሌ እዚያው አገር የነበረችውን በስተርጅና የፀነሰችውን ኤልሳቤጥን ነበር:: “ዘመድሽ ኤልሳቤጥ እርስዋ ደግሞ በእ

ርጅናዋ ወንድ ልጅ ፀንሳለች፤ ለእርስዋም መካን ትባል ለነበረችው ይህ
ስድስተኛ ወር ነው፤ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና" ብሏታል
(ሉቃ. 1÷36)። ኤልሳቤጥ እግዚአብሔር ባይዘገይባት ኖሮ ድንግል ማር
ያም መሲሑን ትፀንስ ዘንድ የሚያስፈልገውን እምነት እንድታገኝ በምሳ
ሌነት ለመጠቀስ ባልበቃች ነበር። ዛሬም እግዚአብሔር የዘገየብን ረስቶን
ሳይሆን በራሱ ጊዜ በመምጣት ለሌሎች እምነት እንድንሆን ሲሆን እንደ
ሚችል ተገንዝበን ልባችንን እናጽና። ዛሬ ብዙዎቻችን ለዎችን ለማጽና
ናት አብርሃምና ሣራን ነው የምንጠቅሰው። ቀላል እንዳልሆነ ቢታወ
ቅም፣ እኛም ለምልክት የሚበቃ ነገር ሊወጣን ይገባል።

## <u>3. ሲቆይ ይጣፍጣል</u>

ያረጀ የወይን ጠጅ ምን እንደሆነ የምናውቅ ይመስለኛል። ያረጀ
የወይን ጠጅ በጣም ትልቅ ግብዣ ነው (ኢሳ. 25÷6)። ከአዲስ ወይን
ጠጅ ይልቅ ያረጀው መጣፈጥ ብቻ ሳይሆን ለማዘጋጀትም ጊዜ ይወስ
ዳል። ያኔ በአብርሃምም ሆነ በካህኑ ዘካርያስ ጊዜም ሆነ ዛሬ ሰዎች በተ
ጋቡ በዓመቱ መውለድ ይጠበቅባቸዋል። የሠርጋቸው ቀን፤ "የዛሬ
ዓመት የማሙሽ አባት፣ የዛሬ ዓመት የማሙሽ እናት" ተብሎም ይዘፈ
ናል። ስለዚህ በተጋቡ በዓመቱ ቢወልዱ አዲስ ነገር አይደለም። ተጋ
ብተው ይተኛሉ፤ ከዚያ ይወልዳሉ። በቃ! ይህ ዜና እንኳን ለመሆን የማ
ይበቃ ነው።

እንደ አብርሃም በ100 ዓመት መውለድ ግን የሚያስደንቅ ብቻ
ሳይሆን፣ የዓለም ድንቃ ድንቆች በሚመዘገቡበት በ"ጊነስ ቡክ ኦፍ ሪከር
ድስ" ላይ የሚመዘገብ ትንግርትና ዜና ነው። ለነዘካርያስም ሆነ ለነአብር
ሃም እግዚአብሔር መዘግየቱ ልጁ የሚያስደስት ያረጀ ወይን ጠጅ እንዲ
ሆን ነው። እንደ ተጋቡ ቢወልዱ ማንም አይደነቅም። እግዚአብሔር ዘግ
ይቶባቸው በስተርጅና መውለዳቸውን የሚሰማ ሁሉ ግን ይሥቃል (ዘፍ.
21÷6)። ምናልባት ይህንን ጽሑፍ የምታነቡ ወገኖች እግዚአብሔር የዘ
ገየባችሁ ቢመስላችሁ ከዚህ ከተራዘመ ጊዜ በኋላ ተራ ነገር ላይወጣችሁ
ይችላል። ያረጀ የወይን ጠጅ ጊዜ እንደሚወስድና ይህም ዋጋ ማስከፈ
ሉን ሳልጠቅስ ግን አላልፍም።

## 4. ዓባይን ያላየ ...

የመጨረሻው ደግሞ እስካሁን ከጠቀስናቸው ሦስት ነጥቦች የሚ
ለይና አሉታዊ የሆነ ነው። አብርሃም ከከለዳውያን ዑር ሲወጣ ይጠብ
ቀው የነበረው ተስፋ ልጅና ምድራዊ ርስትን ነበር። እግዚአብሔር ግን
ለአብርሃም ልጅ የሰጠው ከ25 ዓመት በኋላ ስለነበረ በዚህ በተራዘመ ጊዜ
የአብርሃም አመለካከት ሙሉ በሙሉ ተለወጠ። ስለዚህ ምድራዊ ነገር
መጠበቁን ትቶ ሰማያዊዋን ከተማ ተስፋ ማድረግ እንደ ጀመረ የዕብራ



ውያን ጸሓፊ ይነግረናል (ዕብ. 11÷8-10)። ይህ የሆነው ግን ይስሐቅ ከተ
ወለደ፣ ከዚያም እርሱም በተራው በ60 ዓመቱ ያዕቆብን ከወለደ በኋላ
መሆኑን ከዚሁ ክፍል እንረዳለን። አብርሃም ይህንኑ ለማወቅ በጥቅሉ
ከ85 ዓመት በላይ ሲፈጅበት፣ ለእኛም ይህን ያህል ጊዜ ባይሆን እንኳ
ጊዜ መውሰዱ የማይቀር ነው።

አንዳንዴ ምን መጠየቅ እንዳለብን ካለማወቃችን የተነሣ ጥያቄዎ
ቻችን ተራና ምናምንቴ ሆነው ይገኛሉ። እግዚአብሔር ይህንን ለማስ
ረዳት ቢፈልግም ብዙውን ጊዜ በምንፈልገው ነገር ዐይናችን ስለሚታወር
(ሁለንተናችን ስለሚወለድ) የግድ መዘግየት የሚኖርበት ይመስለኛል።
እርግጥ ነው፤ አንዳንዶቻችን የሚናገረንን ቶሎ ለመረዳት የምንችል
ከሆነ የሚወስድብን ጊዜ ያጥራል። ስለዚህ የማይጠቅም ነገር በመጸለይ
ጊዜያችንን እንዳንፈጅ ጸሎታችን በማስተዋል ቢሆን መልካም ነው።

በአጠቃላይ እስካሁን እንደ ተመለከትነው እግዚአብሔር ያለ ምክ
ንያት አይዘገይም። ሲዘገይም ደግሞ በየትኛውም መልኩ ለመልካም ስለ
ሆነ የተስፋችን ምስክርነት እንዳይናወጥና እግራችን እንዳይንሸራተት እን
ጠንቀቅ። በእርግጥ የእግዚአብሔር መዘግየት በቃላት እንደምንገልጸው
ቀላል አይደለም። ብዙ የሚፈትን፣ እንደ አብርሃም ተስፋ በመቁረጥ ወደ
አጋር የሚገፋፋና ልብን የሚያሳዝን ነው (ምሳ. 13÷12)። ሆኖም በሚያ
ስፈልገን ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ ለማግኘት መቼም ቢሆን ወደ ጸጋው ዙፋን
በድፍረት ለመቅረብ የልጅነት መብት እንዳለን አንዘንጋ (ዕብ. 4÷16)።
ስለ እግዚአብሔር መዘግየት ሳስብ፣ "ከእንግዲህ በቃኝ እልጸልይም፤
ከዚህ በላይ ክንፍ አላወጣ!" ያለችውን አንዲት እኅት አልረሳትም። "እግ
ዚአብሔርን ገና እጠብቅ ዘንድ ምንድን ነኝ?" በማለት የተናገረ ንጉሥም
አለ (2ነገ. 6÷33)።

ምንም እንኳ ሁኔታዎች የተበለሻሹ በሚመስልበት ሁኔታ ውስጥ
ያለን ይመስለን ይሆናል። ሐዋርያው ጳውሎስ ግን፣ "እንደ ተናገረኝ እን
ዲሁ እንዲሆን እግዚአብሔርን አምናለሁና" በማለት የተናገረው እየተለባ
በረች በመጠናቀቅ ላይ በነበረችው ታንኳ ላይ ቆሞ ወደብ አያፏጩበት
ነው (ሐሥ 27÷25)። እርሱ እዚያ ቦታ ሆኖ እንዳመነው እኛም እምነን
መሻገር እንችላለን። እግዚአብሔር በቃሉቹ የታመነ ነውና!

<u>ማስታወሻ</u>

[1] ዳዊት ጸጋዬ፤ ለሻራ (አዲስ አበባ፤ 1993 ዓ.ም) ገጽ 33።

# የነፍስ ትስስር

“ማንም ባሪያዎች ቢያደርጋችሁ ... ትታገሣላችሁና” (2ቆሮ. 11÷20)::

## እውነተኛ የነፍስ ወንድማማቾች

የነፍስ ትስስር በሁለት ሰዎች መካከል ለመልካምም ሆነ ለክፋ ጉድኝት በነፍሳቸው በኩል የሚፈጸም ጠንካራ ትስስር ነው:: የዮናታንና የዳዊት ታሪክ ስመልካሠ የነፍስ ትስስር ምሳሌ ሊሆነን ይችላል:: እርስ በርስ በነፍስ የተሳሰሩ እንደነበር 1ኛ ሳሙኤል 18÷1 እንዲህ በማለት ይናገራል::

“ዳዊትም ለሳኦል መናገሩን በፈጸመ ጊዜ የዮናታን ነፍስ በዳዊት ነፍስ ታሰረች፤ ዮናታንም እንደ ነፍሱ ወደደው::”

በዚሁ ምዕራፍ ቁጥር 3 ላይ ዳዊትና ዮናታን አጅግ በመዋደዳቸው ቃል-ኪዳን አንዳደረጉ እናያለን::

በሁለት ወዳጆች መካከል ያለው የነፍስ ትስስር በጠነከረ ቁጥር ወዳጅነታቸውም ጥልቅና ዘላቂ መሆን ይጀምራል:: የአንዱ የሞራልና የስሜት ብርታት ሌላውን በፈተናው ጊዜ ያጸናዋል:: በድል ጊዜም አብሮ አንዲደሰት ያደርገዋል:: በጓደኛሞች መሐል ያለው ፍቅር በራስ ወዳድነት ያልተበከለና ንጹሕ ከሆነ ትስስራቸው ለመልካም ይሆናል:: ጌታ ኢየሱስ ስለዚህ ዐይነቱ ፍቅር በዮሐንስ 15÷13 ላይ ሲናገር:-

“ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም” ይለናል::

ልክ በዮናታንና በዳዊት፣ በሩትና በኑኃሚን መካከል እንደነበረው ዐይነት ጠንካራና እውነተኛ ወዳጅነት ቢኖር እያንዳንዱ ራሱን የሚጐዳ ቢሆን አንኳ ለሌላኛው ቸር (ለጋስ) እና ታማኝ መሆኑን አያቋርጥም ነበር:: ዮናታን በዳዊት ላይ ያለውን መለኮታዊ ጥሪ ሲያውቅ የእስራኤልን ዙፋን የመውረስ መብቱን ለጓደኛው በፈቃዱ ለመልቀቅ አልተቸገረም:: በተመሳሳይ ሁኔታም ሩት አማቷን ኑኃሚንን ለመከተልና ለማገልገል የወሰነችው ቤተሰቧንና የትውልድ መንደሯን ጥላ እስከ መውጣት ድረስ ነበር::

የዚህ ዐይነት ራስን መሥዋዕት የሚያደርግ የነፍስ ትስስር ለዘላቂ ወዳጅነት፣ ብሎም ስጥሩ ትዳር መሠረት ነው::



አጅግ በቅርበት ከመተሳሰራቸው የተነሣ አንዱ ለሌላኛው ትልቅ መሥዋዕትነት ለመክፈል ፈቃደኛ ስለሆኑ ሁለት ወንድማማቾች የሰማሁት ታሪክ አለ:: ወንድማማቾቹ ወደ አሜሪካ በስደት ሲገቡ፣ ማግኘት የሚችሉትን የትኛውንም ዝቅተኛ ሥራ ከመሥራት በቀር ራሳቸውን የሚደግፉበት ምንም አማራጭ አልነበራቸውም:: አንደኛው አካላዊ ጥንካሬው የጐላ ቢሆንም አእምሮአዊ ዕውቀቱ ብዙም የሚያስመካ አልነበረም:: ሌላኛው ግን በጣም ብልኅና ልበ ብሩህ በመሆኑ፣ ኀይለኛ የሕግ ሰው ለመሆን በሚያበቃ የተፈጥሮ ስጦታ የታደለ ነው:: ባለ ብሩህ እእምሮው ወንድም የሕግ ሰው ለመሆን የሚያበቃውን ትምህርት ሙሉ ጊዜ ሰጥቶ በነጻነት እንዲማር፣ በአእምሮአዊ ዐቅሙ ደከም ያለው ወንድም የተገኘውን ዝቅተኛ ሥራ እየሠራ የሁለቱንም ኑሮ ለመደገፍ ሐሳብ አቀረበ:: ይህኛው ተመርቆ ሥራ ከያዘ በኋላ በሕግ ባለሙያነቱ ሲሳካለት፣ በተራው የሁለቱንም ኑሮ እንዲያስተዳድር ነው የተስማሙት:: አንዳቸው ለአንዳቸው ከነበራቸው ትልቅ ፍቅር የተነሣ ስምምነታቸውን በትክክል ፈጸሙ:: በክፍተኛ የነፍስ ትስስር ስለ ተሳሰሩ አንዳቸው ለአንዳቸው የተሰጡ ስለሆኑና መሥዋዕትነት ለመክፈል ፈቃደኞች ስለ ነበሩ ከግንኙነታቸው ሁለቱም ወንድማማቾች ተጠቅመዋል::

በጥልቅና በንጹሕ ግንኙነትና ትስስር ሁለቱም ነፍሶች አንዳቸው ከሌላኛው ጥንካሬ፣ ብርታት እንዲሁም ዋስትናና ፍቅር ያገኛሉ:: በመክብብ 4÷9-12 ላይ ሰሎሞን የዚህ ዐይነቱን ግንኙነት ባሕርያት (መገለጫዎች) ይዘረዝራል::

“ድካማቸው መልካም ዋጋ አለውና አንድ ብቻ ከመሆን ሁለት መሆን ይሻላል:: ቢወድቁ አንዱ ሁለተኛውን ያነሣዋልና፤ አንዱ ብቻውን ሆኖ በወደቀ ጊዜ ግን የማያነሣው ሁለተኛ የለውምና ወዮለት:: ሁለቱም በአንድነት ቢተኙ ይሞቃቸዋል፤ አንድ ብቻውን ግን እንዴት ይሞቀዋል? አንዱም አንዱን ቢያሸንፍ ሁለቱ በፊቱ ይቆማሉ::”

ሁለት ሰዎች ልባዊ ግንኙነት ሲኖራቸው በእርግጥም ኀይላቸው ይጨምራል:: አንደኛው አንድ ሺህ ሲያሳድድ፣ ሁለቱ በአንድነት ግን ዐሥር ሺህ እንደሚያሳድዱ ዘዳግም 32÷30 ይናገራል:: ሁለት ሰዎች በማናቸውም ነገር ቢስማሙና ቢጸልዩ የሰማዩ አባታቸው የለመኑትን እንደሚሰጣቸው በማቴዎስ 18÷19 ላይ ተነግሮአል::

በኢየሩሳሌም የነበረችው የመጀመሪያዪቱ ቤተ ክርስቲያን ኀይለኛ እና ምርኮን ለመበዝበዝ ብርቱ የነበረችው ሕዝቡ በነፍስ የተሳሰረና ጠንካራ ኅብረት ስለነበረው ነበር::

“ያመኑትም ሕዝብ አንድ ልብ፤ አንዲትም ነፍስ ነበሩአቸው:: ገንዘባቸውም ሁሉ በአንድነት ነበረ እንጂ ካለው አንድ ነገር ስንኳ የራሱ እንደሆነ ማንም አልተናገረም::” (ሐሥ 4÷32)

ኅብረታቸው የጠበቀና ልባቸውም ንጹሕ ስለነበረ ያላቸውን ንብረት በነጻነት ለመጋራት (ለመካፈል) ነጋሪ አላስፈለጋቸውም::

## መለኮታዊ ያልሆነ የጥፋት ትስስር

እርስ በርሳቸው ግልጽ የሆኑ ሁለት በነፍስ የተሳሰሩ ሰዎች የኅብረታቸው ጥንካሬ መሠረት አንዱ ለአንዱ ባለውና በሚሰጠው ቦታ የተወሰነ ይሆናል:: ስለዚህ ከዘመዶቻችን፣ ከሥራ ባልደረቦቻችን፣ አብረውን ከሚኖሩ ወይም አዘውትረን ከምንገናኛቸው፣ ከሚመሩንና ከሚያስተዳድሩን ሰዎች ጋር በነፍስ ልንተሳሰር እንችላለን:: እነዚህ በነፍስ የምንተሳሰራቸው ሰዎች ደግሞ ሕይወታችንንና ጉዟችንን በመቅረጽ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ስለሚችሉ ቤተሰቦቻችንን ጨምሮ ከማን ጋር ኅብረትና ወዳጅነት መመሥረት እንዳለብን ከመወሰናችን በፊት በጥንቃቄ ልንመረምር ይገባናል::

ከሌላ ሰው ጋር ያለን ጉድኝት (ኅብረት) በራስ ወዳድነትና በጥቅም ፈላጊነት የተበከለ ከሆነ፣ በመካከል ያለው የነፍስ ትስስር ራስ ወዳዱ ሰው ሌላኛውን በፈለገው መንገድ እንዲጠቀምበት ያስችለዋል:: የዚህ ምክንያት የአንዳቸው ሐሳብ፣ ፈቃድና ስሜት ለሌላው የተከፈተ ስለሚሆን ነው:: ይህ ዐይነቱ በጽድቅ ላይ ያልተመሠረተ ኅብረት በሌሎች ቀንበር ሥር አውሎን ራሳችንን የሚጐዳ ነገር እንድንናገር ወይም እንድናደርግ ሊጫነን (ሊያስገድደን) ይችላል::

ኀይለኛ (dominant) ግለሰብ የሌላውን ሰው የፈቃድ ኀይል አሸንፎ ጓደኝነት መፍጠር መቻሉ የተለመደ ክንዋኔ መሆኑን ከፍተኛ የሥነ ልቦና ሰዎች ይገልጻሉ:: አንድ ሰው በሌላው ተጽዕኖ ሥር ሊውል ይችላል::

መልካም የሚመስሉ ግንኙነቶች እንኳን የተመሠረቱት እግዚአብሔር በሚያዝዘው አካሄድ ካልሆነ በቀር በመካከል ጥሩ ያልሆነ የነፍስ ትስስር ሊፈጠርና ብሎም ሊያድግ ይችላል::

ማንኛውም ግንኙነት በክርስቶስ ጌትነት ሥር ካልሆነ ወደ ክፉ ትስስር የሚለወጥበት ብዙ መነሻዎች ይኖሩታል:: ለምሳሌ በአማኞች ላይ ብዙ የጋብቻ ቀልድ እንደሚቀለድ እናውቃለን፤ እነዚህ ቀልዶች ግን በበርካታ ትዳሮች ላይ አሳሳቢ ችግር መኖሩን የሚጠቁሙ ናቸው:: ሁለት ሰዎች በጋብቻ ሲጣመሩ ከወላጆቻቸው ጋር ያላቸው የነፍስ ትስስር ካልተሰበረ የኋላ ኋላ ግጭት መፈጠሩ አይቀርም:: የተጋቡ ሰዎች ከወላጆቻቸው ጋር ምንም ዐይነት ግንኙነት አይኑራቸው ማለት ሳይሆን፣ ጠንካራው ትስስራቸው ከትዳር ጓደኛቸው ጋር ሆኖ ለሌሎች ግንኙነቶች የሚኖራቸው ታማኝነትና ግንኙነቶቹ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ አነስተኛ ሊሆን ይገባል:: ግልጹን እንነጋገር ከተባለ፣ የትኛውም ግንኙነት በክርስቶስ ጌትነት ሥር ካልተመሠረተ መለኮታዊ ያልሆነ የነፍስ ትስስር የሚፈጠርበት አጋጣሚ ይኖራል:: የልባችንን የመጀመሪያ ስፍራ እግዚአብሔር ይፈልገዋል:: ከዚያ በመቀጠል የትዳር ጓደኞችን፣ ልጆቻችን፣ ቤተሰባችን እና ባልደረቦቻችን እንደ ቅደም ተከተላቸው ስፍራ ይኖራቸዋል:: ከፍተኛ የነፍስ ትስስራችንን ከእግዚአብሔር ጋር ካደረግን መልካም ያልሆነውን ትስስር የምንቋቋምበት መለኮታዊ ከለላና ብርታት እናገኛለን::



## ይቺ ሥጋ ከሥጋዬ

የነፍስ ትስስር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ "መታሰር" በሚለው ቃል ብቻ ሳይሆን፣ "መጣበቅ" በሚለው ቃልም ተገልጿል:: እግዚአብሔር በሰጠን የደኅንነት ኅብረት በኩል ከእርሱ ጋር የነፍስ ትስስር እንዲኖረን ይፈልጋል::

"አምላክህን እግዚአብሔርን ፍራ፤ እርሱንም አምልክ፤ ከእርሱም ተጣበቅ፤ ..." (ዘዳ. 10÷20) ::

1ቆሮንቶስ 6÷17 "ከጌታ ጋር የሚተባበር ግን አንድ መንፈስ ነው" ሲል፣ ከጌታ ጋር ያለንን መተሳሰር ደግሞ፣ "እኛ ግን የክርስቶስ ልብ አለን (We have the mind of Christ. - NIV)" በሚል አስቀምጧል (1ቆሮ. 2÷16):: አእምሮ (mind) ደግሞ የነፍስ አንድ ክፍል መሆኑ ይታወቃል:: ስለዚህ ከጌታ ጋር ያለን ትስስር በነፍስም በኩል ጭምር ነው::

የነፍስ ትስስር በከፍተኛ ደረጃ የሚገለጸው በጋብቻ ውስጥ ነው:: ሁለት ሰዎች በግብረ ሥጋ ግንኙነት ምክንያት አንድ ሥጋ ሲሆኑ በነፍሳቸው ትስስር ይጀመራል:: እንደ እግዚአብሔር ሐሳብ:- "ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፤ በሚስቱም ይጣበቃል፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ" (ዘፍ. 2÷24)::

አዳምም በዘፍጥረት 2÷23 ላይ "ይህች አጥንት ከአጥንቴ ናት፤ ሥጋም ከሥጋዬ ናት" በማለት ይህንኑ አረጋግጧል:: በሌላ አገላለጽ፣ "ይህች አካል የእኔ ሌላ አካል ናት" ለማለት ነው::

ትዳር ከጌታችን ጋር ያለንን ጥምረት የሚገልጽ የከፍተኛ ግንኙነት ምሳሌ ወይም ሥዕል ነው:: ኢሳይያስ 54÷5 ላይ፤ "ፈጣሪሽ ባልሽ ነው፤ ስሙም የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነው፤ የእስራኤልም ቅዱስ ታዳጊሽ ነው፤ እርሱም የምድር ሁሉ አምላክ ይባላል" ይላል::

ልክ ሁለት ሰዎች በጋብቻ ኪዳን አንድ እንደሚሆኑት እኛም ከጌታ ጋር በደኅንነት ኪዳን አንድ አካል እንደምንሆን ጳውሎስ በኤፌሶን 5÷30፣32 ላይ ይነግረናል፤ "ነገር ግን (የክርስቶስ) የአካሉ ብልቶች

ስለሆንን ... ይህ ምስጢር ታላቅ ነው፤ እኔ ግን ይህን ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተ ክርስቲያን እላለሁ” ብሎናል።

## የወሲብ ወጥመዶች

ከጌታ ጋር ያለን የነፍስ ትስስር ከእርሱ ጋር አንድ እንደሚያደርገን ሁሉ፣ ሁለት ሰዎች በጋብቻ ሲጣመሩ እነርሱም አንድ ይሆናሉ። ይህ ትስስር ኀይለኛ ስለሆነ በተለያየ ጊዜ ርምጃቸው፣ ንግግራቸውና ድርጊታቸው ወደ መመሳሰል ሲመጣ አንዱ የሚጀምረውን ዐረፍተ ነገር ሌላው ሲጨርሰው ይችላል። አንዳንዴም በመልክ የሚመሳሰሉበት ሁኔታም ይኖራል።

በፍቅራቸው ወቅት እንዳቸው የሌላኛውን በጐና መልካም ነገር ቀስመው ከራሳቸው ጋር ሲያዋሕዱ፣ በጥላቻ ጊዜ ደግሞ የሌላኛውን ክፉ ነገር የራሳቸው ያደርጉታል። የዚህ የነፍስ ትስስር ጠንካራ መሆን የጋብቻ ኪዳን እንዲሰበር ተደርጐ እለመፈጠሩን ያሳየናል። ፍቺ በአንድነት የተገመዱ ሁለት ነፍሶችን የሚበጫቅና የሚገነጣጥል የተወገዘ ክፉ ተግባር ነው። ይህም ቢሆን አንድ ላይ በተሰፉት በእነዚህ ነፍሶች ላይ ከባድና የሚያመረቅዝ ቁስል ሳያስከትል ሊለያዩ አይችሉም። ሁለት የዕንጨት ቁርጥራጮች በደንብ በማጣበቂያ ከተያያዙ በኋላ ዕንጨቱን ለመስበር ብንሞክር የሚሰበረው በሌላ አዲስ ቦታ እንጂ መጀመሪያ በተጣበቁበት ስፍራ አለመሆኑ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ይሆናል።

ተጋቢዎቹ የነፍስ ኅብረታቸውን የሚያውጁት በጋብቻቸው ጊዜ በሚፈጽሙት ቃል ኪዳን ቢሆንም አንድ ሥጋና አንድ ነፍስ ወደ መሆን ድምዳሜ የሚያበቃቸው የግብረ ሥጋ ግንኙነት ነው። ይህን በወሲባዊ ውሕደት የሚፈጠር የነፍስ ትስስርን ልዩ የሚያደርገው፣ ሰው ይህንን ጥምረት ከአንድ ሰው ጋር ብቻ እንዲያደርግ ሆኖ መፈጠሩ ነው!

እግዚአብሔር የግብረ ሥጋ ግንኙነትን ሙሉ በሙሉ ማስትም መንፈስ ከመንፈስ፣ ነፍስ ከነፍስ፣ ሥጋ ከሥጋ ጋር እንዲያገናኝን ነው የጀመረው። ጋብቻንም አስደናቂ የሚያደርገው ይህ ጥምረት ነው። እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰውን በዔድን ገነት ሲፈጥር፣ ሴቷን ለመሥራት ግን ከወንዱ አካል መውሰድ ነበረበት። ብሉይ ኪዳን በመጀመሪያ የተጻፈበት የዕብራይስጡ ቋንቋ እንደሚነግረን ሁለቱንም የሚጠራቸው “አዳም” በሚለው ስም ሲሆን፣ የስማቸው አንድ መሆን የኅብረታቸውን ፍጹምነት ያሳያል። ሴቲቱ “ሔዋን”፣ ወንዱ ደግሞ “አዳም” ተብለው በተለያየ ስም የተጠሩት፣ በኀጢአት ከወደቁና ከእግዚአብሔር ጋር ከተለያዩ በኋላ ብቻ ነው።

## የወሲብ ባሮች

የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሁለት ነፍሶችን እንደ አንድ የሚያስተሳስር ከሆነ አንድ ሰው ከጋብቻ ውጭ ዝሙት ቢፈጽም ምን ይሆናል?



የዚህ ሰው ነፍስ አብሯት የግብረ ሥጋ ግንኙነት ከፈጸመው ሁሉ ጋር ትተሳሰራለች። በዚህ ባልተፈቀደ ወሲባዊ ግንኙነት የሚፈጠር መጣበቅ ጥንካሬም ልክ በጋብቻ ኪዳን ውስጥ እንዳለው ሁሉ ብርቱ ይሆናል።

በዚህ ጉዳይ የብዙ ሰዎችን ልምምድ ልንጠቅስ ብንችልም ከቃለ እግዚአብሔር የምናገኘውን ብንይዝ ይመረጣል። ከጋብቻ ውጭ (በፊት) በሚፈጸም ወሲብ በኩል ስለ ተፈጠረ የነፍስ ትስስር ዘፍጥረት 34÷1-3 ላይ እናያለን።

“ለያዕቆብ የወለደችለት የልያ ልጅ ዲናም የዚያን አገር ሴቶች ልጆችን ለማየት ወጣች። የአገሩ አለቃ የኤዊያዊ ሰው የኤሞር ልጅ ሴኬም አያት፤ ወሰዳትም፤ ከእርስዋም ጋር ተኛ፤ አስነወራትም። ልቡናውም በያዕቆብ ልጅ በዲና ፍቅር ተነደፈ። ብላቴናይቱንም ወደዳት፤ ልብዋንም ደስ በሚያሰኛት ነገር ተናገራት።”

በመሠረቱ ሴኬም ዲናን አልወደዳትም፤ ይልቁኑ ከደፈራት በኋላ ነፍሱ (ልቡ) እርሷን መናፈቅና እርሷን መመኘት ጀመረ። እስገድዶ በመድፈር እስነዋሪ ተግባር በኩል ቢሆንም ነፍሶቻቸው ተሳስረዋል። ይሁንንም የሴኬም አባት ኤሞር ለዲና አባት ለያዕቆብ በዘፍጥረት ምዕራፍ 34 በቁጥር 8 ላይ ግልጽ አድርጐታል።

“ልጄ ሴኬም በልጃችሁ ፍቅር ልቡ (the soul of my son - KJV) ተነድፏልና ሚስት እንድትሆነው እባካችሁ እርሷን ስጡት” ብሎ ገልጸለታል።

ጾታዊ (ወሲባዊ) ተራክቦ እንዲህ ዐይነት እስገዳጅና እስጨናቂ የነፍስ ትስስር ስለሚፈጥር ይህንን ግንኙነት ማቆም ያስቸግራል። ይህም ግንኙነት ምን ያህል እንደሚጠነክር የዘፍጥረት መጽሐፍ የሴቷ ፈቃድ ወደ ባሏ ወይም ወደ መጀመሪያ የወሲብ ጓደኛዋ እንደሆነ ይነግረናል።

“ፍላጐትሽም ወደ ባልሽ ይሆናል፤ እርሱም የበላይሽ ይሆናል” (ዘፍ. 3÷16 - እ.መ.ት)።

እንዲት ሴት አብሯት ወሲብ ያደረገውን ሰው ለዳግመኛ ግንኙነት መናፈቅ ብቻ ሳይሆን ታዛዥ ትሆናለች። ከዚህ የተነሣ፣ ተጽዕኖ በሚያሳድሩባቸው ወንዶች ጫናና ግፊት ሴቶች ከእግዚአብሔር ሲርቁ ብዙ ጊዜ ያጋጥማል። ይህ በጣም ያሳዝነኛል።

አንድ የቤተ ክርስቲያናችን አባል የሆነች ሴት የሥራ ባልደረባዋ እግዚአብሔርን የምትፈልግ ስለነበረች ስለ ጌታ ነግራ ወደ ቤተ ክርስቲያን እመጣቻት። ሆኖም ሴቲቱ ሕይወቷን ለጌታ መስጠት እንደምትፈልግ እያለቀሰች ብትናገርም፣ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ምንም ዐይነት ግንኙነት የማይፈልግ ፍቅረኛ ስለነበራት ይህንን ማድረግ አልቻለችም። ከዚህ ሰው ጋር ወሲብ በመፈጸም በሥጋም ሆነ በነፍስ በመተሳሰሯ ለእ

ርሱ ባሪያ የሆነችበትን ስንስለት በጥሳ ነጻነቷን ማወጅ አቃታት:: ይህም እስካሁን እንዳየነው ለበረከት ወይም ለጥፋት ምክንያት ሲሆን ይችላል::

እግዚአብሔር ዓለማትን የፈጠረው ሲታዘዟቸው ነጻነትን፣ ሲጣሱ ደግሞ ጥፋትንና እስራትን በሚያመጡ ተፈጥሯዊና መንፈሳዊ ሕጐች እንዲመሩ አድርጐ ነው:: በቃል-ኪዳን ጋብቻ ሁለት ነፍሶች በአንድነት ለመልካም እንደሚጣበቁ፣ ተጽዕኖና ባርነት ለማምጣትም ሊተሳሰሩ ይችላሉ:: እግዚአብሔር ወሲባዊ ግንኙነትን የፈጠረው በጋብቻ የተጣመሩ ስዎች በእርሱ ፊት አንድ እንዲሆኑ ሲሆን፣ ይህ ሥርዐት ተጥሶ ከጋብቻ በፊትም ሆነ ከጋብቻ ውጭ የሚፈጸም ከሆነ ግን የአንድን ሰው ነፍስ ከብዙዎች ጋር የሚያጣምር ይሆናል::

ብዙ ሰዎች ግን ከጋብቻ በፊት (ውጭ) የሚፈጸመው አስነዋሪ ወሲብ ነፍሳቸውን የሚበታትንና በአንድ ሰው ተወስነው የመኖር ችሎታቸውን እንደሚያበላሽ አልገባቸውም:: የጋብቻ አንዱ ጥቅም የሁለት ሰዎችን የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፍላጐት በነጻነት ማርካት ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ የትዳር ጓደኛሞች አንዱ አንዱን የሚያረካ የማያቋርጥ ፏፏቴና ከሌሎች ጋር የማይጋሩት ጥምን የሚያረካ የውሃ ጉድጓድ እንደሆነ በምሳሌ 5÷15፣ 18-19 ይነግረናል::

"ከራስህ ጉድጓድና ምንጭ ውሃ ጠጥተህ እንደምትረካ፣ ለሚስትህ ታማኝ በመሆንና እርስዋን ብቻ በመውደድ እርካ:: ... ስለዚህ በወጣትነት ያገባሃት ሚስትህ እንደ ጥሩ የምንጭ ውሃ ስለሆነች ትባረክልህ፤ ከእርስዋም ጋር ደስ ይበልህ:: ... ውበትዋ ሁልጊዜ ያርካህ፤ በፍቅርዋም ዘወትር ደስ ይበልህ::" (አዲስ ትርጉም)

ታዲያ አንዱ ለሌላው የወሲብ እርካታ ምንጭ መሆኑን ቢያቋርጥ ምን ይሆናል? ብዙውን ጊዜ ይህ ዐይነቱ ሁኔታ እርካታን ሌላ ቦታ እንዲፈልጉ የሚገፋፋ ፈተናን ያመጣል:: አንድ ሰው በትዳሩ ማግኘት የሚገባውን እርካታ ካላገኘ ወሲባዊ ፍላጐቱን የሚያሟላለት ሌላ የዐልጋ ጓደኛ ፍለጋ ዞር ዞር እንደሚል የተረዳው ሐዋርያው ጳውሎስ አስቀድሞ ይህን አስጠንቅቋል::

"በጸሎት ለመትጋት ሁለታችሁም ተስማምታችሁ ለተወሰነ ጊዜ ካልሆነ በቀር በመለያየት አንዱ የሌላውን የጋብቻ መብት አይከልክል:: በዚህም ምክንያት ራሳችሁን መቆጣጠር አቅቷችሁ ሰይጣን እንዳይፈታተናችሁ እንደገና አብራችሁ ሁኑ::" (1ቆሮ. 7÷5 - አዲስ ትርጉም)

የወሲብ ጥማት በርትቶበት በውስጡ መሞት የጀመረ ሰው እርካታን የሚለግሰው ወዳጅ ሲያገኝ እንደገና በሕይወት ለመኖር ያንሰራራል:: በተደጋጋሚ የሚያመነዝር ሰው ከዚህ የተነሣ መጀመሪያ በደለኝነት አይሰማውም:: እንዲያውም ትክክለኛ ድርጊት እንደፈጸመ የተለያዩ አሳማኝ መሳይ ምክንያቶችን በመደርደር ኀጢአቱን ሊያጸድቅ ይሞክራል



(በተደጋጋሚ ኀጢአት ካልደነዘዘ ግን ውሎ አድሮ የበደለኝነት ስሜት ሊሰማው ይችላል)::

ለመኖር የሚያስፈልገንን መነቃቃት ከጨመረልንና ድብቅ ችሎታችንን ካነሣሣልን፣ አዲስ ፍቅረኛችንን ስናይ የምናገኘውን ደስታ ስናስብ ከጋብቻ በፊት የሚፈጸም ወሲብ (ዝሙት) ልክ እንደሆነ እናስባለን::

ያገቡ ወንዶች አዲሷን ሴት በሕይወታቸው ሁሉ ሲመኟት የነበረች ዐይነት መሆኗንና አስቀድመው ያገቡት ያልፈለጓትን ሴት እንደሆነ ያስባሉ:: ብዙውን ጊዜ ለዝሙት የምንሰጠው የተለያየ ስምና ምክንያት ቢኖረንም ሁልጊዜም ከጋብቻ በፊትም ሆነ ከጋብቻ ውጭ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ብናደርግ ኀጢአትነቱን መሻር አንችልም:: አሳዛኙ ነገር እንደ አጋጣሚና እንደ ቀልድ የሚጀመረው ይህ ወሲባዊ ግንኙነት ምን ዐይነት ከፍተኛ ጥፋት እንደሚያመጣ እምብዛም አለመስተዋሉ ነው::

በ1ኛ ቆሮንቶስ 6÷16፣ 18 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ፣ "አንድ ሰው ከአንዲት አመንዝራ ሴት ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ካደረገ በቅዱሳት መጻሕፍት 'ሁለቱ አንድ አካል ይሆናሉ' ስለተባለ ከሴትዮዋ ጋር አንድ እንደሚሆን አታውቁምን? ... ስለዚህ ከዝሙት ሽሹ፤ ሰው የሚፈጽማቸው ሌሎች ኀጢአቶች ሁሉ ከአካሉ ውጪ ናቸው:: ዝሙትን የሚፈጽም ሁሉ ግን የገዛ አካሉን ይጐዳል:: እንደ ዝሙት ኀጢአት የሰውን አካል የሚያረክስና የሚጐዳ ነገር የለም" ይላል:: (ሕያው ቃል)

ሥጋውን፣ ነፍሱንና መንፈሱን ከሌላ ጋር አጣምሯልና ይህ ሰው ከሌላ የወሲብ ጓደኛው ጋርም በነፍስ የተሳሰረ (አንድ ሥጋ) ነው ማለት ነው:: ይህም እስከ አሁን እንዳየነው ለበረከት ወይም ለጥፋት ምክንያት ሲሆን ይችላል::

አሁንም ቢሆን ከጋብቻ በፊት ወሲብ በመፈጸም አባዜ ተዘፍቀን ከሆነ እንጠንቀቅ:: "እኛ በጣም እንፋቀራለን፤ በቅርብ ደግሞ እንጋባለን፤ ስለዚህ የእኛ ጉዳይ (ግንኙነት) የተለየ ነው" እያልን ራሳችንን መሸንገሉ ለምንም አይበጅም:: በእግዚአብሔርም ዘንድ ተቀባይነት የለውም:: በሕይወታችንም ጥፋትን እንጂ በረከትን አያመጣም::

ሮሜ 11÷16 "በኩራቱም ቅዱስ ከሆነ ቡሆው ደግሞ ቅዱስ ነው፤ ሥሩም ቅዱስ ከሆነ ቅርንጫፎቹ ደግሞ ቅዱሳን ናቸው" ይላል::

በጽድቅና በቅድስና የተጀመረ ግንኙነት ቅዱስና የተባረኩ ቅርንጫፎች ይኖሩታል:: በሌላ ጐኑ ደግሞ በኀጢአትና በርኩስት የተመሠረተ ኅብረት ውጤቱ ክፉ ቅርንጫፍና ፍሬ ሲሆን ይህም መፋታትን፣ አለመተማመንንና ጋጠወጥ ልጆች ማፍራትን የሚያጠቃልል ነው::

## <u>አሁን አድርጉትና ... ለዘላለም ዋጋ ትከፍላላችሁ</u>

በወንድና በሴት መካከል ያለው የግብረ ሥጋ ግንኙነት የማይገመት ኀይል አለው:: እግዚአብሔር በምሳሌ 5÷20-22 ላይ፤

“ልጄ ሆይ፣ ስለ ምን ጋለሞታ ሴት ትወድዳለህ? የሌላይቱንስ ብብት ለምን ታቅፋለህ? የሰው መንገድ በእግዚአብሔር ፊት ነውና፤ አካሄዱንም ሁሉ እርሱ ይመለከታልና፡፡ ኀጥእን ኀጢአቱ ታጠምደዋለች፤ በኀጢአቱም ገመድ ይታሰራል” ያለን ሰዚህ ነው፡፡

እንደ ቀሳል፣ እንደ ዘበት በስሜት በመገፋፋት በተጀመረ ወሲብ የተፈጠረ የነፍስ ትስስር ውጤቱ ሰውን በሕይወት ዘመኑ ሁሉ የሚያስር ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ እግዚአብሔር ሴትን ሲፈጥር መጀመሪያ አብሯት ወሲብ የፈጸመው ወንድ ቀጥሎ ከሚያጋጥሟት ወንዶች ይልቅ በእርሷ ላይ የበላይነት እንዲኖረው አድርጐ ነው፡፡ ስለዚህ ነው ከጋብቻ በፊት ወሲብ መፈጸም እንደማያስፈልግ የሚነገረው፡፡ ስለሆነም ነፍሷም ሆነ መንፈሷ እርሱን ለመንከባከብ፣ ስሜቱን ለማስደሰትና በሕይወት ዘመኑ ሁሉ የእርካታው ምንጭ እንድትሆንለት የተፈጠረች ናት፡፡

ይህን በሚገባ ይገልጸል ብዬ የማስበውን እውነተኛ ታሪክ ልንገራችሁ፡፡ ባለታሪኳ ሜሪ የተባለች ሴት ናት፡፡ ሜሪ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ እያለች ክዳንኤል ጋር ፍቅር ጀመረች፡፡ በዚህ ጊዜ ጌታን ባታውቅም ለወደፊት ባሏ ንጹሕ ሆና መቆየትን የምትፈልግ ሥነ ምግባር ያላት ሴት ነበረች፡፡ ስለዚህ ከእርሱ ጋር ወሲብ መጀመር አልፈለገችም፡፡

ፍቅረኛዋ ዳንኤል ግን፣ “በጣም ስለምንዋደድ፣ ወሲብ ፍቅራችንን የምንገላለጽበት የተለመደ ተፈጥሯዊ ነገር ነው፡፡ እኔና አንቺ ደግሞ አንድ ቀን መጋባታችን አይቀርም” እያለ ዘወትር ይነዘንዛት ስለነበረ በመጨረሻ ተሸነፈች፡፡

ከብዙ ግፊትና ጫና በኋላ አብረው በየጊዜው ወሲብ መፈጸም ጀመሩ፡፡ እንዲህ ሲኖሩ ትምህርቷን ወደ ማገባደዱ ገደማ ጌታን ለመከተል በመወሰኗ ከዚህ በኋላ ከእርሱ ጋር ከጋብቻ በፊት ምንም ዐይነት የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንደማታደርግ አሳወቀችው፡፡ ከዚህም በላይ ወደ ጌታ ልታመጣው በተደጋጋሚ ብትጥርም ዳንኤል ጌታንም ሆነ የክርስትናን የአኗኗር ዘይቤ አለመውደዱ (አለመፈለጉ) ግልጽ ሆነላት፡፡

ሜሪ ትምህርቷን እንደ ጨረሰች ከዳንኤል ጋር ግንኙነቷን አቋረጠች፡፡ ስለዚህ ከእርሱ ትዝታ ለመሸሸና ግንኙነታቸውን ከሚያስታውሷት ነገሮች ለመራቅ ስትል መኖሪያዋን በሌላ ከተማ አደረገች፡፡ በዚያም ለጥቂት ዓመታት ከቆየች በኋላ በፍቅር ከወደቀችለት “ቢል” ከሚባል በጌታ የበረታ ወንድም ጋር ትዳር መሠረተች፡፡

ትዳሯ ከጅማሬው አንሥቶ መልካም ቢሆንም እርሷ ግን ክብረ ንጽሕናዋን የወሰደውንና በሌላ ከተማ የሚኖረውን ለብዙ ዓመታት ያላየችውን የመጀመሪያ ፍቅረኛዋን በማሰላሰል ተቸገረች፡፡ ባሏን ከልቧ ታፈቅረዋለች፤ በውስጧ ግን የቀድሞ ፍቅረኛዋ ይታሰባታል፡፡ ዳንኤልን አሁን ስለማትወደው ለምን እንዲህ ዐይነት ስሜት በውስጧ ሊፈጠር እንደቻለ ራሷም ያልተረዳችው ነገር ነው፡፡



የቀድሞ ሕይወቷን በዝርዝር ለባሏ ነግራ በጌታ ፊት ንስሓ ገብታለች፡፡ ነፍሷ ግን ከዳንኤል ጋር ለመሆን መናፈቋን አላቋረጠችም፡፡ ጉጉቷ እያየለ ሲሄድ ዳንኤልን ብታገኘው ከእርሱ ጋር ሥጋዊ ግንኙነት እንድትፈጥር የሚገፋፋትን ውስጣዊ ግፊት እንደማትቋቋም በመገንዘብ ቤተሰቦቿ ወዳሉበት የድሮ መኖሪያ ከተማ መሄድ እንኳ በጣም ፈራች፡፡

በመጨረሻ ግን ዳንኤል የመጀመሪያ የወሲብ ተጓዳኝዋ ስለሆነ ነፍሷ ከነፍሱ ጋር መተሳሰሯ ገባት፡፡ ከዚያም ከይቅር ባይና አስተዋይ ባለቤቷ ጋር በመሆን በጸሎት ይህንን የነፍስ ትስስር ለመበጠስ (ለማቋረጥ) ቻለች፡፡ ከዚህ ፈውስና ነጻ መውጣት በኋላ ሁለንተናዋን ለባሏ በፈቃዷ መስጠት አላስቸገራትም፡፡ አሁን ከባለቤቷ ጋር ያላት ግንኙነት ከእስከ ዛሬው የተሻለ ልዩ ሲሆን ዳንኤልን ለማሰብም ሆነ ለማየት በውስጧ ምንም ዐይነት እንጥፍጣፊ ምኞት የለም፡፡

በጣሊያን አገር አኩዊላ በምትባል መንደር ውስጥ የሚፈጸም አጉል ባህል አለ፡፡ የዚህች መንደር ሴት ሙሽሮች በሠርጋቸው የመጀመሪያ ምሽት ከመንደሩ ቄስ ጋር ተኝተው ማደር ይጠበቅባቸዋል፡፡

ይህ አስጸያፊ ባህል የተጀመረው ከካህናቱ አንዱ እንዲህ እንዲያደርጉ “ከአምላክ” ዘንድ መገለጥ መቀበሉን ካሳወቀ በኋላ ሲሆን፣ ቀጣዮቹ ካህናት ይህን ባህል ተቀብለው ማስፈጸም ቀጠሉ፡፡

ከዚህ አስቀያሚ ልምምድ የተነሣ በመንደሪቱ ያሉ ሚስቶች ከባሎቻቸው እየተሰወሩ ከካህናቱ ጋር በየጊዜው ግንኙነት እንደሚፈጽሙ ዘገባዎች አመልክተዋል፡፡ ምክንያቱ ግልጽ ነው፤ የመጀመሪያ ወሲባዊ ግንኙነታቸው ከቀሳውስቱ ጋር ስለሆነና ነፍሳቸውም አብራ ስለተሳሰረች ነው፡፡ የእግዚአብሔር ቃል እንደሚናገረው ሁለቱ ወገኖች “አንድ ሥጋ” በመሆናቸው በሴቶቹና በካህናቱ መካከል ምስጢራዊ ኪዳን ተመሥርቷል፡፡ ከላይ እንደገለጽኩት እግዚአብሔር ሴቶችን የሠራው የትዳር ጓደኛቸው መሆን ለሚገባው ለመጀመሪያ ፍቅረኛቸው ጉጉትና ናፍቆት እንዲኖራቸው አድርጐ ነው፡፡

ዘፍጥረት 3÷16 ላይ “ፍላጐትሽም ወደ ባልሽ ይሆናል፤ እርሱም የበላይሽ ይሆናል” (አ.መ.ት) መባሉን ካስታወስን በ2ኛ ጢሞቴዎስ 3÷6 ላይ ሴቶች ቅድስና በሌላቸው ወንዶች በቀላሉ እንደሚታለሉ የተጻፈው ይገባናል፡፡ ይህ ምንባብ፣ “እነዚህ ሰዎች በየቤቱ ሾልከው እየገቡ ብዙ ኀጢአት የተከመረባቸውንና በልዩ ልዩ ፍትወት የሚመሩ፣ መንፈሰ ደካማ የሆኑ ሴቶችን እንደሚያጠምዱት ሰዎች ናቸው፡፡ እንዲህ ዐይነቶቹ ሴቶች ሁልጊዜ ይማራሉ፤ ነገር ግን እውነትን ወደ ማወቅ መድረስ አይችሉም” (አዲስ ትርጉም) ይላል፡፡

በሐሳብ ተለያይተው፣ ወንዱ በንግግር አቁስሏትና ሌላው ቀርቶ አካላዊ ጉዳት ቢያደርስባት እንኳ በነፍስ ስለተሳሰሩ ሴቷ ተለይታው ለመሄድ ብርታቱ አይኖራትም፡፡ እንደገና ተመልሳ ለመምጣት መናፈ

ቋም አይቀርም። አንድ ጊዜ በፍቅር ተሸንፋ ባሪያ ሆናለችና በምንም ሁኔታ ችላው ትኖራለች።

የቤተ ክርስቲያናችን አባል የሆነችው ሱሲ በዐሥራዎቹ መጨረሻና በሃያዎቹ መጀመሪያ ዕድሜዋ ላይ ከአንድ ወጣት ወንድ ጋር በአንዴት ያለ ቀንበር ሥር እንደነበረች በቅርቡ አጫውታኛለች። ከሰውየው ጋር አብረው ይሠሩ ስለነበር ግንኙነታቸውን በጓደኝነት ነው የጀመሩት። አንድ ቀን ግን ኀይለኛ አካላዊ መሳሳብ በመካከላቸው ተፈጠረና ከዚያ በኋላ አብረው መውጣት ጀመሩ። አብረው ለመኖርም ብዙ ጊዜ አልወሰደባቸውም። ግንኙነታቸው ሲቀጥል ግን እርሷን መስደብንና ማንጓጠጥን ሥራዬ ብሎ ተያያዘው። ዋጋ እንደሌላት፣ ጠቃሚ እንዳልሆነችና እስቀያሚ መሆኗን ... እና ስብዕናዋን የሚያንቋሽሹ ሌሎችንም ንግግሮች ይናገራታል። እርሷ ግን እንደምትወደው ስለምታስብ፣ ከምንም ነገር በላይ የምትፈልገው የእርሱን ፍቅርና እንክብካቤ ነበር። ችላ እያላትና ፊት እየነሳት እንኳ፣ ሐሳቡን ቀይሮ ሲፈልጋት በእንብርክኳ ትሄድለታለች። ሆኖም አንድ ቀን ቢፈልጋትም ሌላ ቀን ደግሞ ተፈላጊ ባለመሆኗ ስሜቷ እየተጐዳ መጣ። ከጥቂት ጊዜ በኋላም የምግብ ፍላጐቷ ቀንሶ ሰውነቷ መክሳት ጀመር።

ያቺ ገራገር ወጣት፣ መልከ መልካምና በግልጽ ተናጋሪ የሆነው ይህ ፍቅረኛዋ የሚነግራትን የትኛውንም ነገር ታምናለች። ከእርሷ ውጭ ሌላ ሴት እንደማያውቅ የነገራትንም ተቀብላለች። ሁልጊዜ አንደሚዋሻትና ከእርሷ በዕድሜ ከፍ ከምትል ሴት ጋር ለረጅም ጊዜ አብሮ እንደነበር፣ እንዲሁም እሁንም ድረስ የተለያዩ ሴቶችን እንደሚቀያይር ስታውቅ ግን እጅግ ተደናገጠች። ስለዚህ ትታው ለመሄድ ሞከረች፤ ለረጅም ጊዜ ርቃው መቆየት ግን አቃታት። ነፍሶቻቸው ስለተሳሰሩና ትስስሩም ብርቱ ስለነበር እንደ ፊስገ ሲያሽከረክራትና ከሞላ ጐደል ሁለንተናዋን ሲቆጣጠር አልተቸገረም።

በዚህ መሐል ግን የሱሲ ጓደኛ ጌታን አግኝታ ክርስቲያን ሆነች። ወዲያውኑም ለሱሲ ነጻ መውጣት በመጸለይ ብቻ ሳትወስን፣ በምታገኘው አጋጣሚ ሁሉ ወንጌሉን ትመሰክርላት ጀመር። አንድ ቀን ቤቷ ውስጥ እያሉም ሱሲ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን በማመን የሕይወቷ ጌታ አድርጋ ልትከተለው ወሰነች፤ በመንፈስ ቅዱስም ተጠመቀች። ከዚያም ከእርሱ ጋር የነበራትን አካላዊ ግንኙነት ባታቋርጥም፣ አብራው መኖር አቆመች። ቀስ በቀስ በጌታ መበርታትና ማደግ ስትጀምርም ከትላንት ሕይወቷ ላይ የነበሩትን ነገሮች ጌታ ደረጃ በደረጃ ያነሣላት ጀመር። ግንኙነቷን ሙሉ በሙሉ እንድታቋርጥ አንድ ቀን ጌታ ሲናገራትም ታዘዘችው። ስሜታዊ ትስስሮቿ ግን እንዲህ በቀላሉ የሚቋረጡ አልነበሩም። ሆኖም በጓደኛዋ የማያቋርጥ ጸሎትና ምክር የተነሣ ሱሲ እንደገና ነጻነቷን አገኘች። ከዚያ የጥፋትና የእሥራት ተሞክሮ በስሚቷ፣ በአእምሮዋና በአካሏ ሙሉ በሙሉ ለማገገም ግን ሁለት ሙሉ ዓመታት አስፈልገዋታል።



ማይክል ዳግላስ የተባለ ተዋናይ የሠራው በጊዜው በጣም ዝነኛ የነበረ "**Fatal Attraction**" የተሰኘ ፊልም ማየቴ ትዝ ይለኛል። የፊልሙ ጭብጥ የተመሠረተው ከባለትዳር ወንድ ጋር ለአጭር ጊዜ ግንኙነት ጀምራ ከቆየች በኋላ ሳይታወቃት ከእርሱ ጋር በተፈጠረው ትስስር ስሜቷ ሁሉ ተይዞ ሰውየውን የራሷ ለማድረግ በማሰብ መላ ሕይወቷን መሥዋዕት ባደረገች ሴት ላይ ነው፡

የስሜት እስራቷ ሲያይልባት እርሱን ከመለመን አልፋ ማስፈራራት ጀመረች፤ ትዳሩን ለማፍረስ ጣረች፤ ሚስቱን ፈትቶ ከእርሷ ጋር ግንኙነቱን ለመቀጠል ባለመፈለጉ ከሥራ ሁሉ እንዲባረር ለማድረግ ሞከረች። ከዚህም በኋላ በተስፋ መቁረጥ ተውጣ ልትገድለው ስትጣጣር ለእርሱ ያዘጋጀችው ስለት እርሷኑ ገላገላት። መከራና ልፋቷ ሁሉ በሞት ተደመደመ።

## የተበታተኑ ነፍሶች

ከተለያዩ ሰዎች ጋር በዝሙት የነፍስ ትስስር ያበጁ ሰዎች ምን የሚያጋጥማቸው ይመስላችኋል? ነፍሳቸው ትከፋፈልና ወደ ወሲብ ጓደኞቻቸው ትበታተናለች። ስለዚህ ለትዳር ጓደኞቻቸው ራሳቸውን ሙሉ በሙሉ መስጠት አያችሉም። ሐሳባቸውና ስሜታቸው በየጊዜው ወደ ቀደሙት ፍቅረኞቻቸው ይሸፍታል።

አንድ የቤተ ክርስቲያናችን አገልጋይ በአንድ የጋብቻ ትምህርት ላይ ይህንን እንደሚከተለው ገልጾታል፤ “አንዲት ሴት ከበርካታ ወንዶች ጋር ወሲባዊ ግንኙነት ካላት መንፈሷም ሆነ ነፍሷ እነዚህን ወንዶች ይፈልጋሉ። መንፈሷ ተከፋፍሎ ይበታተናል። ወንዱም ቢሆን የሚገባባትን እያንዳንዷን ሴት እንዲጠብቅ፣ እንዲንከባከብና የሚያስፈልጋትን ሁሉ እንዲያቀርብ ሆኖ ነው መንፈሱ የተበጀው።”

ስለዚህ የወንዱ ነፍስም በአመንዝራነት ምክንያት ልትበታተንና ልትጠፋ ትችላለች። ምሳሌ 6÷27-29፣ 32 ይህንን ይነግረናል። “በጉያው እሳትን የሚታቀፍ፣ ልብሶቹስ የማይቃጠሉ ማን ነው? በፍም ላይ የሚሄድ፣ እግሮቹስ የማይቃጠሉ ማን ነው? ወደ ሰው ሚስት የሚገባም እንዲሁ ነው፤ የሚነካትም ሁሉ ሳይቀጣ አይቀርም። ... ከሴት ጋር የሚያመነዝር ግን አእምሮው የጐደለ ነው፤ እንዲሁም የሚያደርግ ነፍሱን ያጠፋል።”

እንደዚህ ማኅበራዊ እንደሆነ ወሲባዊ ግንኙነት ነፍስን የሚጐዳ ነገር የሚገኝ አይመስለኝም። 1ኛ ቆሮንቶስ 6÷18 እንዲህ ይላል፤ “ከዝሙት ሽሹ። ሰው የሚያደርገው ኀጢአት ሁሉ ከሥጋ ውጭ ነው፤ ዝሙት የሚሠራ ግን በገዛ ሥጋው ላይ ኀጢአትን ይሠራል።”

ከጋብቻ በፊት በሚደረግ ወሲብ ውስጥ ያለፉ ሰዎች ትዳር ከመሠረቱም በኋላ በሐሳባቸውና በስሜታቸው ወደ ቀድሞ ፍቅረኛቸው

መመለስ ብቻ ሳይሆን ከትዳር ጓደኛቸውም ጋር የወሲብ አለመጣጣም ይፈጠርባቸዋል:: አሁን የሚፈጽሙትን ወሲብ ከበፊቱ ጋር ማነጻጸራቸው ስለማይቀርም ሁለንተናቸውን ለትዳር ጓደኛቸው በመስጠት ፍቅር መለዋወጥ ተስኗቸው በወሲብ ለመርካት ሲቸገሩ ይታያሉ::

ስለዚህ ያጡትን (ያቃታቸውን) ፍቅር ሰጥቶ ፍቅር በመቀበል መርካትን ለማግኘት ሲሉ መረን የወጣ ልምምድን ምርጫቸው ያደርጉታል:: ውጭ ውጭ ማየታቸውም የተለመደ ይሆናል:: የዚህ ኀጢአት ተጠያቂ ራሳቸው እንደሆኑ ከቀጣዩ ጥቅስ እንመልከት::

“እያንዳንዱ በራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ይፈተናል:: ከዚህ በኋላ ምኞት ፀንሳ ኀጢአትን ትወልዳለች፤ ኀጢአትም ካደገች በኋላ ሞትን ትወልዳለች::” (ያዕ. 1÷14-15)

ያለፈው የነፍስ ትስስራቸው ያልተቋረጠው፣ ከትላንታቸው ለመላቀቅ፣ እነዚያን ትስስሮች ለመስበርና ስሜታዊ ግንኙነታቸውን፣ ትዝታቸውንና የቀን ሕልማቸውን ለመተው ስላልወሰኑ ነው:: ማኅበራዊ የነፍስ ትስስራቸው ባሕርያቸውን፣ ፈቃዳቸውን፣ ስሜታቸውንና አእምሮአቸውን ስላዳከመው ነጻ ለመሆን መወሰን እንኳ እጅግ አስቸጋሪ ሆኖባቸዋል:: ምሳሌ 6÷32 እንዲህ ይላል፤ “ከሴት ጋር የሚያመነዝር ... ነፍሱን ያጠፋል::”

ምኞትና ኀጢአት ለጊዜው የሚያስደስቱ ቢመስሉም፣ ይህን የሚያደርግ ወደ ኋላ ላይ በዕፍረት፣ በበደለኝነትና በብቸኝነት ስሜት፣ ራስን በመጥላትና ባለመቀበል፣ እግዚአብሔርን በማማረር፣ በሐዘንና በሥቃይ ዋጋ ይከፍላል:: በምኞት እጅግ የተዘፈቀ ሰው ራሱን ብቻ እያታለለ መሆኑን መረዳት ብዙ ጊዜ ይቸግረዋል:: እንዲህ ዐይነቱ ሰው በክህደት ዓለም ውስጥ የሚኖር በመሆኑ ባለፈው ወራዳ ሕይወቱ ስሕተት መሥራቱን መቀበል አይችልም:: ማስተካከል ያለበት የትላንት (ያለፈ) ኀጢአት እንደሌለ ስለሚያስብም የወደፊት ሕይወቱን መለወጥ አይፈልግም:: ሰው በዚህ ምኞት እየተዘፈቀ ከመጣም የሕይወቱን አቅጣጫ ለመለወጥ ይቸገራል:: ከዓመታት በኋላም በኀጢአቱ ምክንያት ለመልካም ነገር ያለው ፍላጐት ስለሚደበዝዝ ለመመለስ ያለው ዕድል በጣም ይጠብባል::

መልካሙ ዜና ግን፣ ሰው የወደቀበት የምኞትና የኀጢአት አዘቅት ምንም ያህል ቢከፋ፣ ጌታን በሙሉ ልብ ለመከተልና ለማገልገል ቁርጥ ውሳኔ ካደረገ በእግዚአብሔር ርዳታ ነጻ መውጣት መቻሉ ነው::

## <u>በዝሙት (በወሲብ) የሚተላለፉ መናፍስት</u>

በወሲባዊ ግንኙነት የሰው ነፍስ ምን ያህል ሲከፋፈል እንደሚችል እስካሁን ተመልክተናል:: ከዚህ የባሰ አውዳሚና ዋጋ የሚያስከፍል ውጤት ሲኖረው እንደሚችልም መናገር እፈልጋለሁ:: ሰው የሚያደር



ገው ኀጢአት ሁሉ ከሥጋ ውጭ ቢሆንም ዝሙትን የሚሠራ ግን በገዛ ሥጋው ላይ ኀጢአት እንደሚሠራ ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 6÷15-16 ላይ መናገሩን አስታውሱ:: ሐዋርያው ጳውሎስ ማመን ያቃተው በሚመስል መልኩ የሚከተለውን ተናግሮአል፤

“ሥጋችሁ የክርስቶስ ብልቶች እንደሆነ አታውቁምን? እንግዲህ የክርስቶስን ብልቶች ወስጄ የጋለሞታ ብልቶች ላድርጋቸውን? አይገባም! ወይስ ከጋለሞታ ጋር የሚተባበር አንድ ሥጋ እንዲሆን አታውቁምን? ‘ሁለቱ አንድ ሥጋ ይሆናሉ’ ተብሏልና::” ሁለት ሰዎች እንሰሳ በመጋፋፍ አንድ ሥጋ ከሆኑ፣ ርኩሳን መናፍስት ከአንዳቸው ወደ ሌላኛው ሊተላለፉ መቻላቸው ግልጽ ከሆኑት የዚህ ኀጢአት ውጤቶች መካከል አንደኛው ነው::

ክርስቲያን ከክርስቶስ ጋር አንድ ነውና ባልተቀደሰ ግንኙነት ራሱን ለማርከስ ማሰቡ ለጳውሎስ አስደንጋጭ ነው የሆነበት::

ስለዚህ ሌላኛው የዝሙት አስከፊ ውጤት ደግሞ የሚከተለው ነው:: ሁለት ሰዎች በግብረ ሥጋ ግንኙነት አንድ ሥጋ ሲሆኑ፣ ርኩሳን መናፍስት ከአንዱ ወደሌላኛው ሊተላለፉ (ሊሸጋገሩ) ይችላሉ::

ግብረ ሰዶማውያንን በማማከር በማገልገልበት ጊዜ የተረዳሁት ነገር፣ ተመሳሳይ ጾታ ያላቸውን ሰዎች መናፈቅና መመኘት የጀመሩት በሕፃንነታቸው ወይም በወጣትነታቸው ጊዜ ተመሳሳይ ጾታ ባለው ሰው በደረሰባቸው የወሲብ ጥቃት የተነሣ መሆኑን ነው:: ግብረ ሰዶማዊነታቸው የዚህ ቀጥተኛ ውጤት ነው:: ለጥቃት በተጋለጡበት በዚያ ወቅት የግብረ ሰዶማዊነት መንፈስ እንደተላለፈባቸው እገነዘባለሁ:: ያም መንፈስ በውስጣቸው ሆኖ ሌሎችን ወደ ራስ መሳብ ይጀምራል:: የግብረ ሰዶማዊነት መንፈስ ጠንካራ መንፈስ በመሆኑ፣ መንፈሳዊና ስሜታዊ እርዳታ ሳያገኙ በራሳቸው ነጻ መሆን የሚችሉት ጥቂቶች ብቻ ናቸው:: ግብረ ሰዶማውያን አንዳንዴ ሊቋቋሙት በማይችሉት ሁኔታ በብርቱ እንደሚሳሳቡ አምናለሁ::

አንድ ጓደኛዬ አጐቱ የስምንት ዓመት ልጅ እያለ በወንድሙ ወሲባዊ ጥቃት እንደ ደረሰበት አጫውቶኛል:: ካደገ በኋላ ከተቃራኒ ጾታ ጋር ጋብቻ መሠረትና የተረጋጋ ኑሮ ለመኖር ቢወስንም አልቻለም:: ከሚስቱ ጋር በነበረው ጋብቻ በተፈጠረው የነፍስ ትስስር በኩል የመናፍስት ሽግግር በመኖሩ ምክንያትም እርሱም ሆነ ሚስቱ በተመሳሳይ የግብረ ሰዶማዊነት መንፈስ ጫና ሥር ወደቁ:: ስለዚህ አንዳቸው ለሌላኛው ታማኝ መሆን ስላልቻሉ ከዐሥራ አራት ዓመታት የአብሮነት ኑሮ በኋላ ትዳራቸው ፈረሰ:: ሚስቱ ሌላ ሴት፣ ወንዱም ሌላ ወንድ ተከትለው ሄዱ:: ይህ ሰው በወንድሙ ልጅ ላይ የወሲብ ጥቃት አደረሰ:: የወሲባዊ ጥቃትና የግብረ ሰዶማዊነት ሰንሰለቱ በዚያ መከረኛ ቤተሰብ ላይ ከትውልድ ትውልድ እየተላለፈ (እየተራባ) ነው! “የዘር ናቸው” የምንላቸው

# የእግዚአብሔር ፊት

የኢትዮጵያን ታሪክ ከሃይማኖት ነጥሎ ማየት ያስቸግራል። ስለዚህ አዳዲስ ነገሥታት ወደ ዙፋን በወጡ ቁጥር የሃይማኖት መግለጫ የመጀመሪያ ተግባራቸው ይሆናል። ከእነዚህ የኢትዮጵያ ነገሥታት መካከል የጐንደሩ ዐፄ ፋሲል አንደኛው ነበሩ። ዐፄ ፋሲል ወደ ዙፋን የመጡት አባታቸው ዐፄ ሱስንዮስ የካቶሊክ እምነት ተከታይ መሆናቸው ባስነሣው የሃይማኖት ጦርነት ምክንያት ነው።

ዐፄ ፋሲል እንደ ነገሡ የካቶሊክ እና የኦርቶዶክስ ሃይማኖት መሪዎች የየራሳቸውን ሲቃውንት ሰብስበው ለክርክር ጐንደር ከተማ ላይ ጉባኤ ተደረገ። የተለያዩ ጥያቄዎች እየተነሡ ክርክሩ ተካሄደ። የካቶሊኩ ተወካይ፣ "የእግዚአብሔር ፊቱ ወዴት ነው?" የሚል ጥያቄ አቀረበ። የኦርቶዶክሱ ተወካይ ዕጨጌ በትረ ጊዮርጊስ በጉባኤው መብራት አስበርተው፣ "የዚህ መብራት ፊቱ ወዴት ነው?" በማለት መልሰው ጠየቁት። ለዚህ መልስ ሲታጣ ዕጨጌው፣ "የዚህ መብራት ፊት 'በዚህ ገጽ ነው' እንደማይባል፣ የእግዚአብሔርም ፊት በአራቱ ማዕዘን ነው" በማለት አብራሩ። ከዚያም ድንገት ፊታቸውን አዞሩና የካቶሊኩን መሪ በጥፊ መቱት (የተለመደ "ኦርቶዶክሳዊ" አካሄድ!)። ጥፊው ከወንጌሉ አካሄድ ጋር ሙሉ በሙሉ እንደሚጋጭ ታሪክ ጸሐፊው ተክለ ጻድቅ መኩሪያም ይመሰክራሉ።[1] ስለ እግዚአብሔር ፊት የተሰጠው መልስ ግን አስደስቶኛል። እስቲ ስለ እግዚአብሔር ፊት እንነጋገር።

"እግዚአብሔር ፊቱን ያብራልህ፤ ይራራልህም፤ እግዚአብሔር ፊቱን ወደ አንተ ያንሣ፤ ሰላምንም ይስጥህ" (ዘኍ. 6÷25-26)። ይህ የእስራኤልን ሕዝብ እንዲባርኩበት ለአሮንና ለልጆቹ በሙሴ በኩል ከእግዚአብሔር የተሳለፈ ጥልቅ ምስጢር ያለው የበረከት ትእዛዝ ነው። ስለ እግዚአብሔር ፊት ለመረዳት ስለ ፊት የተነገሩ ጥቂት ገለጻዎችን ከመጽሐፍ ቅዱስ መመልከት ያስፈልገናል። ስለዚህ የሰውን ፊት ስለ ማየት የተጻፉ አንዳንድ ክፍሎችን ለአብነት እንመልከት።

የእስራኤል የመጀመሪያ ንጉሥ የነበረው ሳኦል ሲሞት ዳዊት በይሁዳ ላይ ነገሠ። በመላው እስራኤል ላይ ይነግሥ ዘንድ ሕጋዊ ወራሽነቱ ተቀባይነት እንዲያገኝ በልቡ ያሰብና ይናፍቅ ነበር። ስለዚህ ጠቅላላው የእስራኤል ሕዝብ የዳዊትን ንግሥና እንዲቀበሉ የሳኦል የጦር አለቃ አበኔር ለድርድር እንደሚመጣ ሲነግረው ዳዊት እንደሚደሰት አያጠራጥርም። የንጉሥ ልጅ የሆነችውንሜልኮልን መልሶ ካገባ ደግሞ ምኞቱ በቀላሉ እንደሚሳካለትና ዙፋኑም እንደሚረጋጋ ዳዊት ገብቶታል። ስለዚህ አበኔርን፣ "ፊቴን ስማየት በመጣህ ጊዜ የሳኦልን ልጅ ሜልኮልን ካላመጣህልኝ ፊቴን አታይም" አለው (2ሳሙ. 3÷13)። "ፊቴን አታይም!" ማለት ከባድ ማስፈራሪያ ነው! ስለዚህ ነገሥታት ይህን በመጠቀም ሲያስፈራሩ ኖረዋል።



የዳዊት ልጅ አቤሴሎም ወንድሙን አምኖንን ገድሎ ወደ ጌሹር ከኰበለለ በኋላ ምሕረት ተደርጐለት ተመለሰ። ነገር ግን፣ "ወደ ቤቱ ይሂድ እንጂ ፊቴን እንዳያይ" ብሎ ንጉሡ ዳዊት በማዘዙ አቤሴሎም በምሕረት ቢመለስም የንጉሡን ፊት እንዲያይ አልተፈቀደለትም (2ሳሙ. 14÷24)። ከሁለት ዓመታት ጭንቀት በኋላ፣ አቤሴሎም የንጉሡን ፊት አለማየቱ ከሌሎች ቅጣቶች ሁሉ የማይቻል ስለሆነበት፣ "የንጉሡን ፊት ልይ፤ ኀጢአት ቢሆንብኝ ይግደለኝ" እስከ ማለት ደረሰ (14÷32)። አቤሴሎም በኢየሩሳሌም የአባቱን ፊት ሳያይ ለሁለት ዓመታት መቀመጡ በጣም ስላስመረረው፣ "ለምን ከጌሹር መጣሁ?" በማለት አጠንክሮ ይጠይቅ ነበር። ጌሹር በኀጢአቱ ጊዜ የተሸሸገበትና ምሕረት እስኪያገኝ የተደበቀበት ስፍራ ነበር። እኛም የሰማዩ አባታችንን ፊት የማናይ ከሆነ፣ "የአባቴን ፊት የማላይ ከሆነ ለምን ... ?" ብለን ራሳችንን መጠየቅ አለብን። "ሁልጊዜ ፊቱን ፈልጉ" (መዝ. 105÷4) የተባለው ለዚህ ይሆን?

መጽሐፈ አስቴር እንደሚነግረን ሐማ በንጉሡ አርጤክስስ ፊት በታላቅ ክብርና ሞገስ ሲያገለግል የቆየ ባለሟል ነው። የተለያዩ ሕጐች እንዲወጡ ለማስደረግ ንጉሡን ለማሳመን የሚያስችል ተሰሚነትም ነበረው። በዚህ መልኩ በትጋት ቢያገለግልም በአንድ ስህተት ምክንያት፣ የንጉሡን ፊት እንዳያይ "የሐማን ፊት ሸፈኑት" እና ሰቅለው ገደሉት (7÷8)። የንጉሥን ፊት ማየት በንጉሥ ፊት ሞገስ ላገኙ ሰዎች ብቻ የተፈቀደ ነው።

ከላይ በአጭሩ እንደ ተመለከትነው የንጉሥንም ሆነ የአባትን ፊት ማየት ሞገስና በረከት የማግኘት ትርጉም ሲኖረው፣ የንጉሥን ፊት አለማየት ደግሞ የቅጣት፣ የእርግማንና ሞገስ የማጣት ምልክት ነው። ለእኛ "እግዚአብሔር ፈራጃችን ... እግዚአብሔር ሕግ ሰጪያችን ... እግዚአብሔር ንጉሣችን" ነውና (ኢሳ. 33÷22) ፊቱን ለማየት የምንጓጓለት ምድራዊ ንጉሥ አይኖረን ይሆናል። ሆኖም የምድር ነገሥታትን ፊት ማየት ይህን ከመሰለ፣ የሕያው እግዚአብሔርን ፊት ማየት ምን ሲሆን እንደሚችል መረዳት አያዳግተንም።

"እግዚአብሔር ፊቱን ያብራላችሁ" የሚለው ቀላል በረከት አይደለም። ምክንያቱም እግዚአብሔር ፊቱን ሲያበራ ሰላምና ደኅንነት ይሆናል (መዝ. 80÷3)። ፊቱን ሲሰውር ግን አደጋ ነው። "ፊትህን ስትሰውር ይደነግጣሉ፤ ነፍሳቸውን ታወጣለህ ይሞታሉም፤ ወደ ዐፈራቸ

እባብ ብትነድፍ ለደጋሚው ትርፍ የለውም'' (*መክ.* 10÷11) ብሎ እንደ መሰሰለት የተናገረው ትውስ ይለኛል:: የጠላትን ሐሳብ ከእርሱ ቀድመን ካላፈረስን በቀር የኋለኛው ውጊያችን አሰልቺና አድካሚ፣ ምናልባትም ውጤት አልባ ሊሆንብን ይችላል::

የክርስቶስ ኢየሱስ መወለድ በሌሊት *መንጎቻቸውን* ይጠብቁ ለነበሩ እረኞች በ*መጀመሪያ* የተነገረው፣ ሰው ሁሉ ባንቀላፋበት ሰዓት እነርሱ በንቃት *መንጎቻቸውን* ይጠብቁ ስለነበር ነው:: ቀን ሳለ እንኳ መንቃት ላቃታቸውና ለሚያንቀላፉ የእግዚአብሔር ቤት እረኞች ይህ ትምህርት የሚሰጥ ይመስለኛል:: እረኞቹም የምሥራቹን እንደ ሰሙ ወዲያውኑ የተነገራቸውን ለማየት ሄደዋል (*ሉቃ.* 2÷8-15):: በሄዱ ጊዜ ግን *መንጎቻቸውን* ይዘው መሄዳቸው አለመጠቀሱ አውሬና ወንበዴ በሚበዛበትና ጨለማው በከበደበት ሌሊት እንኳ በ*መንጎቻቸው* ላይ ጥቃት እንደማይደርስ ምን ያህል ልበ ሙሉ እንደ ነበሩ ያስረዳናል:: *መታመናቸው* በሥጋ ጥበባቸው ላይ ብቻ አልነበረም:: በሌሊት *መንቃትና* የእግዚአብሔርን ፊት መፈለግ ማንም ያልሰማውን የምሥራች በቅድሚያ ለመስማት ካስቻለና በእግዚአብሔር ላይ ያለንን *መታመን* ካሳደገልን ከዚህ በኋላ ፊቱን የማንፈልግበት ምን ምክንያት ይኖረናል?

እንግዲህ ምድራችን አሁን ካለችበት የከፋ መከራ ሳያጋጥመንና ሕይወታችን ከዚህ የባሰ ሳይበዘበዝ ወደ እግዚአብሔር ፊት በጸሎት መመለስ አለብን:: የቀኑን ፊት ሳናይ፣ የአለቆቻችንን ፊት ሳናይ፣ የወዳጆቻችንን ፊት ሳናይ የአምላካችንን ፊት እንፈልግ:: እኛ የእርሱን ፊት ለማየት ከምንፈልገው ይበልጥ የሰማዩ አባታችንም እንድንቀርበውና ሕይወታችን በፊቱ ብርሃን እንዲሞላ ይናፍቃልና እናፍርም:: ይህን የተባረከ ልምምድ በሕይወት ዘመናችን ሁሉ ቸል እንዳንል እንጠንቀቅ::

እግዚአብሔር ፊቱን ያብራልን፤ ይራራልንም:: እግዚአብሔር ፊቱን ወደ እኛ ያንሣ፤ ሰላምንም ይስጠን:: አሜን!

<u>ማስታወሻ</u>

[1] ተክለ ጻድቅ *መኩሪያ*፤ *የኢትዮጵያ ታሪክ - ከዐፄ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ* (አዲስ አበባ፤ 1961) ገጽ 140-142::



## <u>ዋቢ ጽሑፎች</u>


ማሞ ውድነህ፤ *አሉላ አባነጋ* (አዲስ አበባ፤ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፤ 1979 ዓ.ም)::

ሰለሞን ዴሬሳ፤ *ልጅነት* (አዲስ አበባ፤ 1962 ዓ.ም)::

በእውቀቱ ስዩም፤ *ኗሪ አልባ ጐጆዎች* (አዲስ አበባ፤ 1995 ዓ.ም)::

ብርሃኑ ነጋ (ዶ/ር)፤ *የነጻነት ጎህ ሲቀድ : ሊቀለበስ የተሞከረው የኢትዮጵያ ዲሞክራሲ* (ከቃሊቲ እስር ቤት፤ አዲስ አበባ፤ ግንቦት 1998 ዓ.ም)::

ተክለ ጻድቅ *መኩሪያ*፤ *የኢትዮጵያ ታሪክ - ከዐፄ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ* (አዲስ አበባ፤ 1961 ዓ.ም)::

*አዲስ አድማስ ጋዜጣ*፤ አድማስ አድቨርታይዚንግ ኃ.የተ.የግ.ማ.፤ ልዩ የሚሊኒየም እትም፤ ጳጉሜ 6 1999 ዓ.ም::

*አዲስ ነገር ጋዜጣ*፤ መስፍን አሳታሚ ሚያዝያ 11 ቀን 2000 ዓ.ም እትም::

ከበደ ሚካኤል፤ *ታላላቅ ሰዎች* (አዲስ አበባ፤ 1960 ዓ.ም)::

__________፤ *የቅኔ ውበት* (አዲስ አበባ፤ 1961 ዓ.ም)::

ኮሊን ማንስል (ቄስ)፤ *ትምህርተ ክርስቶስ፤ አጠቃላይ የነገረ መለኮት ትምህርት 2ኛ መጽሐፍ* (አዲስ አበባ፤ 1999 ዓ.ም)::

የታላቁ ተልዕኮ አገልግሎት፤ *ተልዕኮአችን መጽሔት የ25ኛ ዓመት በዓል የመታሰቢያ እትም* (ኅዳር 1998 ዓ.ም)::

የታላቁ ተልዕኮ አገልግሎት፤ *የጽድቅ ፀሐይ መጽሔት* ልዩ እትም (ኅዳር 1995 ዓ.ም)::

ደረጀ በላይነህ፤ *የዕድሜ መንገድ* (አዲስ አበባ፤ 1997 ዓ.ም)::

ዳዊት ጸጋዬ፤ *አሻራ* (አዲስ አበባ፤ 1993 ዓ.ም)::

ጌትነት እንየው፤ *ዕውቀትን ፍለጋ* (አዲስ አበባ፤ 1994 ዓ.ም)::

ጳውሎስ ኞኞ፤ *አጤ ምኒልክ* (አዲስ አበባ፤ 1984 ዓ.ም)::

*ፈርጥ መጽሔት*፤ ሜጋ ኪነ ጥበባት ማዕከል፤ ቁጥር 23 ሰኔ 1993 ዕትም::

Bilquis Sheikh with Richard Schneider. *I Dared To Call Him Father*. The Miraculous Story Of A Muslim Woman's Encounter With God (life Journey, 2004).

*Britannica's Concise Pictured Encyclopaedia Volume 4* (Chicago, Overseas Edition,1967).

*Britannice's Concise Pictured Encyclopaedia Volume 5* (Chicago, Overseas Edition,1967).

Dunn, Ronald. *Don't Just Sit There ... Have Faith* (England, Alpha Books)

__________. *Don't Just Stand There ... Pray Something : The Incredible Power Of Intercessory Prayer* (England, Thomas Nelson Pub., 1992)

Greenwold, Gary. *Seductions Exposed: The Spiritual Dynamics Of Relationships (Eagle's Nest Publishers, 1998).*

*Herper's Bible Dictionery* (New York, Harper & Brothers, 1952).

Hinn, Benny. *The Anointing (Ben Publishing,1992).*

Lisitzky, Gene. *Thomas Jefferson* : A Man Who Changed the World (Pyramid Books , New York) 1967.

Oxford Advanced Learner's Dictionary, Sixth Edition (Oxford University Press).

Prince, Derek. *Husbends & Fathers: Rediscover The Creator's Purpose For Men (Sovereign World 2000).*

*The Complete Works of Williem Shakespeare (London, Spring Books ,1970).*

*The NIV Study Bible* (Michigan, Zondervan Publishing House, 1985).

*The History Of Our World (Boston, Houghton Mifflin Company 1961).*

# የጸሓፊው ቀደምት ሥራዎች

## የዘላለም ኪዳን:-
(The Better Covenant)



ዕምቅ የሆነውን የቃል ኪዳን ምስጢር መግዘ፣ የሳላ ወንብ የሚያጠብቅ እውነት የጨበጠና በሕይወታችን ከሚያልፈው ለልፍ የተነዛ የፈዘዘብንን የተሰሩ ቃል ዳግም የሚያድስ ነው። የአዲሱ ኪዳን መርሖዎችንም ፍንትው አድርጎ በማጉላት የተለወጠ የሕይወት አቀጣጫን የሚጠቁም ኮምፓስ በውስጡ የያዘ መጽሐፍ!

ደራሲ:- ዋችማን ኒ
የገጽ ብዛት: 140
ዋጋ: 12.00

## የጋብቻ ኪዳን:-
(The Marriage Covenant)



ትዳርን ክሩት ሆነን እንደ እንክን-የለሽ ገነት ለምናይ አሊያም ደግሞ ውስጡ ገብተን ከሲኦል የባሰ ቃጠሎ ለሆነብን፣ ዴሪክ ፕሪንስ ካለፉበት የሕይወት ልምድ ጋር አጋምደው የተሳካ ትዳርን ምስጢር ያቀረቡበት መጽሐፍ!

ደራሲ:- ዴሪክ ፕሪንስ
የገጽ ብዛት: 64
ዋጋ: 6.50



## የተሸነፈ ዓለም
(Love Not the World)



ዋና አሳቡ የዓለምን ዕርቃን መግለጥና ከግልጠቱ በስቲያ ቀኖችን ማርኮ እንዴት መጠቀም እንደሚቻል መጠቆም ነው፤ የዓለምን ዕድፍና ጉድፍ፣ ውበትና መዓዛ አሳይቶ ከእጃችን ላይ ሳሙናውን ያስቀምጥልናል - ለካስ ዕድፉን አንጽቶ መጠቀም የእኛ ድርሻ ነውና! ይህ መጽሐፍ በዚህ ብቻ አይደለም የሚገርመው፤ ቤተ ክርስቲያን ግቢ ውስጥ አየታከክን፣ ከአጥር ውጭ ራአይ እንዳይኖረን የሚያደርገንን ጸሊም ድባብ ከመጽሐፍ ቅዱስ አጥር ያልዘለለ አሳብ ቁልጭ ባለና በጥሩ ቃና እያመጣ ይሸረክትልናል።

ደራሲ:- ዋችማን ኒ
የገጽ ብዛት : 88
ዋጋ: 8.50

## የጸጋው ብርታት
(Changed into His Likeness)




ሦስቱ አዕማዶች (አብርሃም፣ ይስሐቅና ያዕቆብ) ፈቃዳቸውን ለአምላካቸው አስገዝተው ያለፉባቸው የሕይወት ጠመዝማዛ መንገዶች ተሞክሮ ለእኛ ዛሬ ይጠቅሙን ዘንድ ጸሐፊው በቅደም ተከተል አስቀምጧቸዋል።
ብዙ ጊዜ ለጌታ ኢየሱስ ተለይተን በቅድስና ለመኖር ወስነን ሳለ፣ ድንገት ኬላ ጥሰን በከሳሽ ግራ ለተጋባን መጽሐፉ መልስ አለው።
ጸጋ የሚባለውን ቃል በጭንቅላታችን እንጂ በልባችን ለማናውቀው የጸጋው ብርታት በጠብታ እንደሚወርድ ግሉኮስ የእግዚአብሔርን ደግነት እያንጠባጠበ ውስጣችንን ያበረታል።

ደራሲ:- ዋችማን ኒ
የገጽ ብዛት: 120
ዋጋው: 10.50

## <u>የእምነት ኃይል</u>
**(Don't Just Sit there ... Have Faith)**



በሚገርሙ የእግዚአብሔር ሰዎች ጥያቄና ጉድ በሚያሰኝ የጌታ መልስ የታጀበው ይህ መጽሐፍ፣ ከዘመነ-አብርሃም ጀምሮ የክርስቶስ ኢየሱስን ደም ወዳጠቀሰው የሞትና የትንሣኤው ኃይል ዘመን ድረስ ዘልቆ፤ እምነት እንደ ቀቤ ሲናጥ፣ ... እንደ አበባ ሲፈካ፣ ደግሞ ሲጠወልግ ፍንትው ያደርጋል። እንደ ትራፊክ መብራትም ይመስላል፤ ቀይ ያበራና ያቆማል፤ በአረንጓዴ ያከንፋል። እናም ይህን መጽሐፍ ያነበበ አገልጋይና ምዕመን ያለ ምንም ጥርጥር ከጌታ አዲስ ነገር ሲጠብቅ በውስጡ አዲስ ቀን ያረግዛል።

ደራሲ፡- ሮናልድ ደን
የገጽ ብዛት : 156
ዋጋ: 13.00

## <u>የዕረፍት ሕይወት</u>
**(Sit, Walk, Stand)**



"ከክርስቶስ ጋር በሰማያዊ ስፍራ እንዴት መቀመጥ እንዳለብንና ለእርሱ እንደሚገባ እዚህ ታች (በምድር ላይ) እንዴት መመላለስ እንዳለብን ማወቅ ይኖርብናል፤ ነገር ግን በጠላት ፊት እንዴት መቆም እንዳለብንም ደግሞ ማወቅ አለብን!!" ስለዚህ ከእግዚአብሔር፣ ከዓለም እና ከዲያብሎስ ጋር የሚኖረንን ግንኙነት ባሕርይ በኤፌሶን መልዕክት ላይ ከተመሠረተው ከዚህ መጽሐፍ በቀላሉና በግልጽ ያገኙታል።

ደራሲ፡- ዋችማን ኒ
የገጽ ብዛት፡ 64
ዋጋው፡ 6.65

**እግዚአብሔር ይባርክዎ!**